በኵሉ ምድር ወበኵሉ ትውልደ ምድር ፤

ለልጅ ልጅ ዘመን በዚህ ዓለም ሁሉ እውነተኛ ልጅ ያስነሣል፤

ወይትአመር ስምየ ወስምከ በመትሕተ ሰማይ በኵሉ መዋዕል፤

በዘመኑ ሁሉ በሰማይ በታች ባለ በዚህ ዓለም የእኔም ያንተም ስም ይጠራል ።

፳፤ ወሑር ወልድየ በሰላም ፤

ልጄ ! በዘመኑ ሁሉ በተድላ በደስታ ኑር ፤

ያጽንዓከ አምላክ ልዑል አምላኪየ ወአምላክከ ለገቢረ ፈቃዳቲሁ ፤

የኔም ያንተም ገናና ፈጣሪ የሆነ ፈቃዱን ለመፈጸም አጽንቶ ያኖርኃል ፤

ወይባርክ ኵሎ ዘርዐከ ወተረፈ ዘርዕከ ለትውልደ ትውልድ ዘለዓለም በኵሉ በረከተ ጽድቅ ፤

ልጅህን የልጅ ልጅህን ፈጽሞ ለዘለዓለም ያከብራል ፤

ከመ ትኩን ለበረከት በኵሉ ምድር፤

ባገኘህበት በዓለም ሁሉ ለዘለዓለም የከበርህ ትሆን ዘንድ ፤

ወወጽአ እምኀቤሁ እንዘ ይትፌሣሕ ይስሐቅ ፤

ይስሐቅም ደስ እያለው ከአባቱ ዘንድ ወጣ።

## ምዕራፍ ፲፱

፩፤ ወኮነ በቀዳሚ ሱባዔ በዘ፵ ወ፬ቱ ኢዮቤልዩ በካልዕ ዓመቱ ፤

በመጀመርያው ሱባዔ በ፵፬ተኛው ኢዮቤልዩ በሁለተኛው ዓመት ፤

ወውእቱ ዓመት በዘሞተ አብርሃም፤

ይኸውም አብርሃም የሞተበት ዘመን ነው ፤

መጽኡ ይስሐቅ ወእስማኤል እምዓዘቅተ መሐላ ፤

ይስሐቅና እስማኤል ከቤርሳቤህ መጡ ፤

ከመ ይግበሩ በዓለ ሱባዔ ዛቲ በዓል በቀዳሚ ማዕረር ኀበ አብርሃም አቡሆሙ ፤

በሱባዔ የምትከበር ይህችን በዓል ከማክበር አስቀድሞ ያከብሩ ዘንድ ወደ አባታቸው አብርሃም መጡ።

፪፤ ወተፈሥሐ አብርሃም እስመ ፪ሆሙ ደቂቁ መጽኡ ኀቤሁ ፤

አብርሃምም ሁለቱ ልጆቹ ስለ

መጡ ደስ አለው ፤

እስመ ብዙኀ ጥሪቱ ለይስሐቅ በቤርሳቤህ ፤

በቤርሳቤህ ያለ የይስሐቅ ገንዘቡ ብዙ ነበርና

ወየሐውር ይስሐቅ ወይዋሂ ጥሪቶ፤

ይስሐቅ ገንዘቡን ይጎበኝ ዘንድ ይኼድ ነበር ፤

ወይገብዕ ኀበ አቡሁ አብርሃም ፤

ጎብኝቶም ወደ አባቱ አብርሃም ይመለስ ነበር።

፫፤ ወበዝ መዋዕል መጽአ እስማኤል ይርአይ አባሁ ፤

በዚህ ወራት እስማኤል አባቱን ያይ ዘንድ መጣ፤

ወመጽኡ ኵሎሙ ኅቡረ ፤

ሁሉም አንድ ሁነው መጡ።

፬፤ ወጠብሐ ይስሐቅ መሥዋዕተ ለጽንሐሕ ፤

ይስሐቅም ስቡን ለማጤስ መሥዋዕት ሠዋ ፤

ወአዕረገ ዲበ ምሥዋዕ ዘገብረ አቡሁ በኬብሮን ፤

አባቱ በኬብሮን በሠራው መሠዊያ ላይ መሥዋዕቱን አቀረበ፤

ወሠዐ መሥዋዕተ መድኃኒት ፤

ድኅነት ያለው መሥዋዕትን ሠዋ ፤

ወገብረ ግዝአ ፍሥሐ በቅድመ እስማኤል እኁሁ ፤

በወንድሙ በእስማኤል ፊት ደስ የሚአሰኝ ፍሪዳ አቀረበ።

፭፤ ወገብረት ርብቃ ዳፍንተ ሐዲሰ እምሥርናይ ሐዲስ ፤

ርብቃ ከአዲሱ ስንዴ መል ካም ትኩስ እምባሻ ጋገረች ፤

ወወሀበቶ ለያዕቆብ ወልዳ ከመ ያብእ እምቀዳሚ ፍሬ ምድር ፤

ለአባቱ አብርሃም ያቀርብ ዘንድ መጀመሪያ ከደረሰው ስንዴ ለልጇ ለያዕቆብ ሰጠችው ፤

ከመ ይብላዕ ወይባርክ ፈጣሬ ኵሉ ዘእንበለ ይሙት ፤

ሳይሞት በልቶ ፈጣሪውን ያመሰግን ዘንድ።

፮፤ ወይስሐቅኒ ውእቱ ፈነወ በእደ ያዕቆብ ዘይሤኒ መሥዋዕተ መድኃ ኒት አብርሃም ይብላዕ ወይስተይ፤

ይስሐቅም አብርሃም ይበላ ይጠጣ ዘንድ ያማረ የተወደደ

ድኅነት የሚደረግበት መሥዋ ዕትን በያዕቆብ እጅ ሰደደለት፤

ወበልዐ ወሰትየ ወባረኮ ለአምላክ ልዑል ዘፈጠረ ሰማየ ወምድረ ፤

በልቶ ጠጥቶ ሰማይን ምድ ርን የፈጠረ ፤

ወኵሎ ስፍሐ ምድር ፤

ምድርን ሁሉ የፈጠረ ልዑል ባሕርይ አምላክን አመሰገነ ፤

ወወሀቦሙ አብርሃም ለውሉደ ሰብእ ይብልዑ ወይስተዩ ፤

አብርሃምም ይበሉ ይጠጡ ዘንድ ለሰው ሁሉ ልጆች ሰጣ ቸው ፤

ወባረኩ ፈጣሪሆሙ ፤

ይበሉ ይጠጡ ዘንድ ሰጥቷቸዋ ልና ፈጣሪያቸውን አመሰገኑ፡፡

፯፤ ወይቤ አብርሃም ይእዜኒ እት ኃነይ ለከ አምላኪየ አነ ፤

አብርሃምም እንዲህ አለ ፤ አሁን ፈጣሪየ ላንተ እገዛለሁ፤

እስመ አርአይከኒ ዛተ ዕለተ ፤

ይህችን ቀን አሳይተኸኛልና፤

ወናሁ አነ ወልደ ፻፸ወ፭ቱ ክረምት፤

እነሆ እኔ የ፻፸፭ ዘመን ሰው ነኝ ፤

ወልሀቁ ፤

አርጅቻለሁ፤

ወፍጹመ መዋዕል፤

ዘመኔ ሁሉ ተፈጽሟል ፤

ወኵሎን መዋዕልየ ኮናኒ ሰላመ ፤

ዘመኖቼ ሁሉ ተድላ ደስታ ሆኑልኝ ፤

ሰይፈ ጸላዒ ኢሞዓኒ ፤

የጠላት የዲያብሎስ ሥልጣን ድል አልነሣኝም አለ፡፡

፰፤ ወበኵሉ ዘወሀብከኒ ፤

በሰጠኸኝ ሁሉ ፤

ውሉድየ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትየ እስከ ዛቲ ዕለት ፤

በልጆቼም ባለ ዘመኔ ሁሉ እስከዚች ቀን ድረስ ፤

ይኩን አምላኪየ ሣህልከ ላዕለ ገብርከ ፤

ፈጣሪዬ ይቅርታህ በእኔ በባሪ ያህ ላይ ይሁን ይደረግ፤

ወላዕለ ዘርዓ ውሉዱ ፤

በልጅ ልጆቼ ላይ ይሁን ፤

ከመ ይኩንከ ሕዝበ ኅሩየ ፣

የተመረጠ ወገን ይሆንህ ዘንድ፣

ወርስተ እምኵሉ አሕዛበ ምድር ፣

በዚህ ዓለም ከሚኖር ከአሕዛብ ተለይቶ ማደርያህ ይሆን ዘንድ ፣

እምይእዜ ወእስከ ኵሉ መዋዕል ዘትውልደ ምድር ለኵሉ ዓለማት፣

ከዛሬ ጀምሮ በዚህ ዓለም የተወለደ ልጅ እስከሚኖርበት ዘመን ድረስ።

፱፣ ወጸውዖ ለያዕቆብ ወይቤሎ፣

ያዕቆብን ጠርቶ እንዲህ አለው፣

ወልድየ ያዕቆብ ይባርከ አምላከ ኵሉ ፣

ልጄ ያዕቆብ ሁሉን የፈጠረ አምላክ ያክብርህ ፣

ወያኀይልከ ለገቢረ ጽድቅ ወፈቃዱ በቅድመ ዚአሁ፣

በሱ ፊት ፈቃዱን ለመፈጸም በጎ ሥራ ለመሥራት ያበርታህ ፣

ወይኅረይ ብከ ወበዘርዕከ ከመ ትኩንዎ ሕዝበ ለርስቱ ፣

እንደ ፈቃዱ ማደርያው ልትሆን ባንተም በልጆችህም ኃይልን ያሳድርባችሁ ፣

በከመ ፈቃዱ በኵሉ መዋዕል ፣

በዘመኑ ሁሉ እሱ እንደወደደ።

፲፣ ወአንተኒ ወልድየ ያዕቆብ ቅረብ ወሰዐመኒ ፣

አንተም ልጄ ያዕቆብ ቀርበህ ሳመኝ ፣

ወቀርበ ወሰዓሞ ፣

ቀርቦ ሳመው።

፲፩፣ ወይቤ ቡሩክ አንተ ወልድየ ያዕቆብ ፣

ልጄ ያዕቆብ ልዑል ነህ ክቡር ነህ ፣

ወኵሎሙ ውሉደ እግዚአብሔር ልዑል በኵሉ ዓለማት ፣

የልዑል እግዚአብሔር ልጆች ሁሉ በዓለም ሁሉ ክቡራን ናቸው ፣

ወየሀብከ እግዚአብሔር ዘርዐ ጽድቅ እምውሉድከ ፣

መሥዋዕት የሚሠዋ ምግባር ትሩፋት የሚሠራ ልጅ ይስጥህ

ወይትቀደስ በማዕከለ ኵሉ ምድር፣

በዓለም ሁሉ ይከብር ዘንድ ከልጆችህ ሁሉ የእውነት ልጅ ይስጥህ፣

ይትቀነዩ ለከ አሕዛብ ፣

አሕዛብ ይገዙልህ ፣

ወይስግዱ በቅድመ ዘርእከ ኵሎሙ አሕዛብ ፣

ይወድቁ ታሕቴከ ሲል ነው ፣ አሕዛብ ሁሉ በልጆችህ ፊት ይንበርከኩ ፣

ወኩን ኃያለ በቅድመ ሰብእ እንዘ ትሜብል ውስተ ኵሉ ዘርአ ሴት፣

በሴት ልጆች ሁሉ መካከል ሠልጥነህ በሰው ሁሉ ፊት ኃይለኛ ሁን።

፲፱፣ ወአሜሃ ይጸድቃ ፍናዊከ ፣

ያን ጊዜ ሥራህ ሁሉ እውነተኛ ይሆናል ፣

ወፍና ውሉድከ ለከዊነ ሕዝብ ቅዱስ ፣

ክቡር ወገን ለመሆን የልጆችህ ሥራ ሁሉ የቀና ይሆናል ፣

ወየሀብከ አምላክ ልዑል ኵሎን በረከታተ እለ ባረከኒ ፣

እኔን የመረቀባቸውን ምርቃቶችን ሁሉ ልዑል አምላክ ይስጥህ፣

ወእለ ባረኮሙ ለኖኅ ወለአዳም ያዕርፉ ዲበ ድማኀከ ፣

ኖኅን አዳምን የመረቀው ምርቃት በላይህ ላይ ይደር ፣

ለቅዳሴ ዘርዕከ ኵሉ ትውልደ ትውልድ ፣

በልጅ ልጅህ ዘመን ሁሉ ልጆችን ለማክበር፣

ወእስከ ለዓለመ ዓለም ፣

እስከ ዘለዓለምም ድረስ በአንተ ይደር።

፳፣ ወያንጽሕከ እምኵሉ ርስሐት ወርኵስ ፣

በነቢብ በገቢር ከሚሠራው ኀጢአት ያነጻሕ ዘንድ ፣

ከመ ታስተሥሪ እምኵሉ አበሳ ዘበኢያእምሮ ገገይከ ፣

ባለማወቅ ከበደልኸው ኃጢአት ወገን ታስተሠርይ ዘንድ ፣

ወየኃይልከ ወይባርከ ፣

ያበርታህ ያክብርህ ፤

ትረስ ኵላ ምድረ ፤

ሀገሩን ምድሩን ሁሉ ትወርስ ዘንድ ፤

ወየሐድስ ኪዳኖ ምስሌከ ከመ ትኩኖ ሕዝበ ቅዱሰ ለርስቱ በኵሉ ዓለማት ፤

በዓለም ሁሉ ለማደሪያው ልዩ ወገን ትሆን ዘንድ መሐላውን ካንተ ጋር ያጽና፡፡

፲፬፤ ወውእቱ ይኩንከ ለከ ወለዘርዕከ አምላክ ዘበህልው ወዘበጽድቅ በኵሉ መዋዕለ ምድር ፤

ምድር ጸንታ በኖረችበት ዘመን ሁሉ እሱ ላንተም ለልጆችህም በውነት በህልውና ጸንቶ የሚኖር ፈጣሪ ይሁንህ፡፡

፲፭፤ ወአንተኒ ወልድየ ያዕቆብ ተዘከር ቃልየ ፤

ልጄ ያዕቆብ አንተም ቃሌን አስብ ፤

ወዕቀብ ትእዛዛተ አቡከ አብርሃም፤

የአባትህ አብርሃምን ትእዛዝ ጠብቅ ፤

ወተፈለጥ እምአሕዛብ ፤

ከአሕዛብ ተለይ፤

ወኢትብላዕ ምስሌሆሙ ፤

ከነሱ ጋር አትብላ ፤

ወኢትግበር በከመ ምግባሪሆሙ ፤

የነዚያን ሥራ አትሥራ ፤

ወኢትኩን ሎሙ ቢጸ ፤

ባልንጀራቸውም አትኹን ፤

እስመ ግብሮሙ ርኩስ ፤

ሥራቸው የተነቀፈ ነውና ፤ የነዚያ ጓደኛ አትሁን ፤

ወኵሉ ፍናዊሆሙ ግሙን ወምኑን ወሰቈራር መሥዋዕቶሙ፤

ሥራቸውም መሥዋዕታቸውም የተናቀ የማይወደድ ነውና፡፡

፲፮፤ ለአብድንት ይዘብሑ ፤

መሥዋዕታቸውን ለጣዖት ይሠዋሉ ፤

ወለአጋንንት ይሰግዱ ፤

ለአጋንንት ይሰግዳሉ ፤

ወበውስተ መቃብራት ይበልዑ ወይሰትዩ ፤

በመቃብርም ይበላሉ ይጠጣሉ፤

ወኵሉ ግብሮሙ ከንቱ ወበክ ፤

ሥራቸው ሁሉ ከንቱ ብላሽ ነው ፤

ወአልቦሙ ልብ ለሀልዮ ፤

ለማሰብም ልብ የላቸውም ፤

ወኢኮነ አዕይንቲሆሙ ዘይሬኢ ፤

ዓይናቸው የሚያይ አይደለም፤

ምንት ግብሮሙ ፤

ሥራቸው ምድነው?

፲፯፤ ወእፎ እሙንቱ ይስሕቱ እንዘ ይብሉ ለዕፀ አንተ አምላኪየ ፤

እንጨቱን አንተ ፈጣሪየ ነህ እያሉ እንዴት ይስታሉ?

ወለዕብን አንተ እግዚእየ ፤

ድንጋዩንም አንተ ጌታዬ ነህ እያሉ፤

ወአንተ መባልሕየ ፤

የምታድነኝ አንተ ነህ እያሉ ፤

ወኢሀሎ ልብ ፤

እንዲህ ለሚስት ሰውም እውቀት የለውም ፤

ወኢይሰምዖሙ ፤

አይሰማቸውም ፤

ወኢያድኅኖሙ፤

አያድናቸውም።

፲፰፤ ወአንተኒ ወልድየ ያዕቆብ አምላክ ልዑል ይርዳእከ ፤

ልጄ ያዕቆብ አንተን ግን ልዑል እግዚአብሔር ይርዳህ፤

ወአምላከ ሰማይ ይባርከ ፤

ሰማይን የፈጠረ እግዚአብሔር ያክብርህ ፤

ወያግኅሥከ እምነ ርኵሶሙ ወእምነ ኵሉ ስሕተቶሙ ፤

ከስሕተታቸውም ከኃጢአታቸውም ሁሉ ያርቅህ።

፲፱፤ ወተዐቀብ ወልድየ ያዕቆብ ከመ ኢትንሣእ ብእሲተ እምኵሉ ዘርዐ አዋልደ ከነአን ፤

ልጄ ያዕቆብ ከከነዓን ልጆች ወገን እዳትጋባ ተጠንቀቅ ፤

እስመ ኵሉ ዘርዖሙ ለሥራዌ እምድር ፤

ልጆቻቸው ሁሉ ከዚህ ዓለም ለመጥፋት ተዘጋጅተዋልና ፤

እስመ በአበሳ ካም ስሕተ ከነአን ፤

በካም በደል ከነአን ስቷልና ፤

ወኵሉ ዘርዑ ይደመሰስ እምድር፤

ልጁ የልጅ ልጁ ሁሉ ከዚህ ዓለም ይጠፋል፤

ወዘይድኅን አልቦ እምኔሆሙ አመ ዕለተ ደይን ፤

ቁርጥ ፍርድ በሚፈረድበት ቀን ከነዚህ የሚድን የለምና ከከነዓን ልጆች ወገን ሚስት አታግባ።

፳፤ ወለኵሎሙ እለ ያመልኩ ጣዖተ ወለጽሉአን አልቦሙ ምንትኒ ተስፋ በምድረ ሕያዋን ፤

የተጠሉ ጣዖትን የሚያመልኩ ሁሉ በጻድቃን ሀገር በገነት ምንም ምን ተስፋ የላቸውምና፤

እስመ ውስተ ሲኦል ይወርዱ ፤

ወደመቃብር ወደሲኦል ይወርዳሉና ፤

ወውስተ መካነ ደይን የሐውሩ ፤

ጽኑ መከራ ቁርጥ ፍርድ ወደ አለበት ሲኦል ይወርዳሉ፤

ወአልቦሙ ምንትኒ ዝክር በዲበ ምድር ፤

በዚህ ዓለም ምንም ምን ስም አጠራርመታሰቢያ የላቸውም፤

ከመ ተነሥኡ ውሉደ ሰዶም እም ድር ከማሁ ይትነሥኡ ኵሎሙ እለ ያመልኩ ጣዖተ ፤

የሰዶም ልጆች እንደጠፉ በዚህ ዓለም ጣዖትን የሚያመልኩ ሰዎች ሁሉ ይጠፋሉ።

፳፩፤ ኢትፍራህ ወልድየ ያዕቆብ፤

ልጄ ያዕቆብ አትፍራ ፤

ወኢትደንግፅ ወልደ አብርሃም ፤

የአብርሃም ልጅ ሆይ አትደ ንግጥ ፤

አምላክ ልዑል ይዕቀብከ እምነ ሙስና ፤

ልዑል እግዚአብሔር ከጥፋት ይጠብቅህ ፤

ወእምኵሉ ፍኖተ ስሕተት ውእቱ ይባልሕከ ፤

ከስሕተት ሥራ ሁሉ እሱ ያድንኀ።

፳፪፤ ወዘንተ ቤተ ሐነፅኩ ሊተ ከመ አንብር ስምየ ላዕሌሁ በዲበ ምድር ፤

በዚህ ዓለም ስሜ በሱ ላይ ይጠራ ዘንድ ይኸንን ቤት ሠራሁ ፤

ተውህበት ለከ ወለዘርዕከ ይእቲ በረከት እስከ ለዓለም ፤

ይህች በረከት ላንተም ለልጆ ችህም ለዘላለም ተሰጠች።

፳፫፤ ወትሰመይ ቤተ አብርሃም ለዓለመ ዓለም ፤

ለዘለዓለሙ የአብርሃም ቤት ትባላለች ፤

እስመ አንተ ተሐንጽ ቤትየ ፤

ቤቴን አንተ ታንጻለህና ፤

ወታቀውም ስምየ ቅድመ አምላክ እስከ ለዓለም ፤

ለዘለዓለም ስሜን በአምላክ ፊት ታጸናለህ ፤

ወዘርዕከ ወስምከ ይቀውም ውስተ ኵሉ ትውልደ ምድር፤

ልጅህ ስምህ በዚህ ዓለም በልጅ ልጅህ ጸንቶ ይኖራል፤

ወአኅለቀ አብርሃም እንዘ ይኤዝዞ ወእንዘ ይባርኮ ፤

አብርሃምም እሱን አዝዞ መርቆ ጨረሰ።

፳፬፤ ወሰከቡ ፪ሆሙ ኅቡረ ውስተ አራት አሐቲ ፤

ሁለቱም አንድ ሁነው በአንዲት አልጋ ላይ ተኙ ፤

ወኖመ ያዕቆብ ውስተ ሕፅነ አብርሃም አበ አቡሁ ፤

ያዕቆብም ከአባቱ አባት አብርሃም አጠገብ ተኛ፤

ወሰዐሞ ስብዐ ፤

፯ት ጊዜ ሳመው

ወተፈሥሐ፤

ደስ አለው ፤

እስመ ምሕረቱ ወልቡ ላዕሌሁ ፤

ይቅርታው አሳቡ በሱ ላይ ነበርና ፤

ወባረኮ በኵሉ ልቡ ፤

በፍጹም ልቡናው ሁሉ መረቀው አመሰገነው።

፳፭፤ ወይቤ አምላክ ልዑል አምላከ ኵሉ ፤

ገናና አምላክ የምትሆን የሁሉ አምላክ ፤

ወፈጣሬ ኵሉ ፤

የሁሉ ፈጣሪ ፤

ዘአውጻእከኒ እምነ ዑር ዘከላውዴዎን ፤

ከከላውዴዎን ውስጥ ከዑር ያወጣኸኝ ፤

ከመ ተሀበኒ ዛተ ምድረ ከመ እረሳ ለዓለም ፤

ለዘላለሙ እወርሳት ዘንድ ይህ ችን ሀገር የሰጠኸኝ ፣

ወከመ አቅም ዘርዐ ቅዱሰ ከመ ይትባረክ ለዓለም ፣

ለዘለዓለሙ ይከብር ዘንድ ክቡር ልጅን እንድወልድ ከዑር ያወጣኸኝ።

፳፮፤ ባርኮ ለያዕቆብ ወልድየ ፣

ልጄ ያዕቆብን አክብረው ፣

ዘበኵሉ ልብየ አፈቅሮ ወዘበም ሕረትየ በእለ ይትፌሣሕ ቦቱ ልብየ እባርኮ ፣

በሱ ደስ በሚላቸው በፍጹም ልቡናየ የምወደው በበረከቴ የምመርቀው ያዕቆብን አክብረው አለው ፣

ወይኩን ሣህልከ ወምሕረትከ ነዋኀ ላዕሌሁ ፣

ይቅርታህ ቸርነትህ በሱ ላይ ብዙ ይሁን ፣

ወላዕለ ዘርኡ ኵሎ መዋዕለ ፣

ባለ ዘመኑ ሁሉ ለርሱ ለልጆቹም ይብዛ ይደረግ ፣

ኢትኅድጎ ወኢትትሐየዮ እምይእዜ ወእስከ መዋዕል ለዓለም ፣

ከዛሬ ጀምሮ ለዘላለሙ አትለየው ቸልም አትበለው።

፳፯፤ ወይኩና አዕይንቲከ ክሡታተ ላዕሌሁ ወላዕለ ዘርዑ ፣

ዓይኖችህ እሱን ልጆቹን ይመልከቱ ፣

ከመ ይዕቀብዎ ፣

ይጠብቁት ዘንድ ፣

ወከመ ትባርኮ ወትቀድሶ አንተ ለሕዝብከ ዘለርስትከ ፣

ማደርያህ የሚሆን ወገንህን አንተ ታከብረው ታበዛው ዘንድ፣

ወባርኮ በኵሉ በረከታቲከ እምይእዜ ወእስከ ኵሉን መዋዕል ዘለዓለም ፣

ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በበረከትህ ሁሉ አክብረው።

፳፰፤ ወሐድስ ኪዳነከ ወሣህለከ ምስሌሁ ወምስለ ዘርዑ በኵሉ ፈቃድከ ወበኵሉ ትውልደ ምድር፣

በዚህ ዓለም በሚኖሩ ሁሉ በፍጹም ፈቃድህ መሐላህን ይቅርታህን ከሱም ከልጁም ጋራ አድርግ አለ ፤

ወአንበረ አብርሃም ፪ኤሆን አጻብዓ ያዕቆብ ዲበ አዕይንቲሁ ፤

በያዕቆብ ጣት ራሱን አማወተ አኖረ ፤

ወባረኮ ለአምላከ አማልክት ፤

ከአማልክት በላይ የሆነ የካህ ናት ፈጣሪን አመሰገነው፤

ወከደነ ገጾ ፤

ፊቱንም ሸፈነ።

ምዕ ፲፯

፩፤ ወሰፍሐ እገሪሁ ፤

እግሩን ዘረጋ ፤

ወኖመ ንዋመ ዘለዓለም ፤

የዘለዓለም እንቅልፍን ተኛ ማለት ሞተ፤

ወተጋብአ ኀበ አበዊሁ ፤

በሞት ወደ አባቶቹ ሄደ ፤

ወበዝ ኵሉ ሀሎ ያዕቆብ ይሰክብ ውስተ ሕፅኑ ፤

በዚህ ሁሉ ጊዜ ያዕቆብ ባጠገቡ ተኝቶ ነበረ ፤

ወኢያእመረ ከመ ሞተ አብርሃም አበ አቡሁ፤

ያባቱ አባት አያቱ አብርሃም እንደሞተ አላወቀም ነበር።

፪፤ ወነቅሐ ያዕቆብ እምንዋሙ፤

ያዕቆብም ከእንቅልፉ ነቃ ፤

ወናሁ ቈረ አብርሃም ወኮነ ከመ በረድ፤

እነሆ አብርሃምን ቀዝቅዞ እንደ በረዶ ሆኖ አገኘው ፤

ወይቤ ያዕቆብ አባ አባ ፤

ያዕቆብም አባቴ አባቴ አለ ፤

ወአልቦ ዘነበቦ ፤

የመለሰለት ቃል የለም ፤

ወአእመረ ከመ ሞተ አብርሃም ፤

ያዕቆብም አብርሃም እንደሞተ አወቀ።

፫፤ ወተንሥአ እምሕፅኑ ወሮፀ ወነገራ ለእሙ ርብቃ ፤

ያዕቆብም ካጠገቡ ተነሥቶ ፈጥኖ ሄዶ ለናቱ ለርብቃ አባቴ አብርሃም ሞተ ብሎ ነገራት ፤

ወሖረት ርብቃ ኀበ ይስሐቅ ሌሊተ ወነገሮ ፤

ርብቃም ሌሊት ሄዳ ለይስ

ሐቅ አባትህ ሞተ ብላ ነገረ
ችው ፤

ወሖሩ ኀቡረ ወያዕቆብ ምስሌሆሙ፤

ርብቃ ይስሐቅ ሔዱ ያዕቆ
ብም ከነሱ ጋር ሄደ ፤

ወማኅቶት ውስተ እዴሁ ፤

ያዕቆብ በእጁ መብራቱን ይዞ
ነበር ፤

ወሐዊሮሙ ረከብዎ ለአብርሃም
እንዘ ይሰክብ በድኑ ፤

በሔዱም ጊዜ አብርሃም ሙቶ
እሬሳው ተጋድሞ አገኙት ፤

ወወድቀ ይስሐቅ ውስተ ገጸ አብር
ሃም ወበከየ ፤

ይስሐቅ በአባቱ አብርሃም ፊት
ወድቆ አለቀሰ ፤

ወሰዓሞ ፤

ስሞ ተሰናበተው።

፬፤ ወቃል ተሰምዐ በቤተ አብርሃም፤

በአብርሃም ቤት ልቅሶ ተሰማ፤

ወተንሥአ እስማኤል ወልዱ ወሖረ
ኀበ አብርሃም አቡሁ ፤

እስማኤል ልጁ ተነሥቶ ወደ
አባቱ አብርሃም ሄደ ፤

ወበከዮ ለአብርሃም አቡሁ ፤

ለአባቱ ለአብርሃም አለቀሰለት፤

ውእቱ ወኵሉ ቤተ አብርሃም በከዩ
ብካየ ዓቢየ፤

እሱ የአብርሃም ወገኖች ሁሉ
ጽኑ ልቅሶ አለቀሱ ፤

ወቀበርዎ ውስተ በአተ ካዕበት ቅሩብ
ሳራ ብእሲቱ ፤

ሁለት ክፍል በምትሆን በሚ
ስቱ ሳራ አጠገብ ዕጥፍነት
ባላት ዋሻ ቀበሩት ፤

ወውሉዱ ይስሐቅ ወእስማኤል
በከዩ ፵ መዋዕለ ፤

ልጆቹ ይስሐቅና እስማኤል
አርባ ቀን አለቀሱ፤ ያርባ ቀን
ፍታት ምሳሌ ነው ፤

ወኵሉ ሰብአ ቤቱ ፤

ቤተሰቦቹም ሁሉ አለቀሱለት።

፭፤ ወይስሐቅ ወእስማኤል ፤

የእስማኤል የይስሐቅ ቤተ
ሰቦች ሁሉ አለቀሱ ፤

ወኵሉ ውሉዶሙ ወውሉደ ኬጡራ
በመካኖሙ በከዩ ፤

ልጆቻቸው የኬጡራ ልጆች
ሁሉ በቦታቸው ኹነው አለቀ
ሱለት፤

ወተፈጸመ ላሀ ብካየ አብርሃም ፤

የአብርሃም ልቅሶ ሐዘን ተፈ ጸመ።

፲፯፤ ወ፫ተ ኢዮቤልወ ሐይወ ፤

ሦስት ኢዮቤልዩ ኖረ ፤

ወ፬ተ ሱባዔ ዓመት ፤

ዐራት የዘመን ሱባዔ ፤

፻ተ ወ፸ወ፭ተ ዓመተ ኮነ ፤

፻፸፭ ዘመን ኖረ ፤ ሰባው ዘመን አንድ ኢዮቤልዩ ሁኖ ፵፱ ዘመን ይተርፋል፤ ፵፱ዱ ፫ት ሱባኤ ይሆናል፤ ፩ቱን ዘመን ከ፭ቱ ሲጨምሩት አንድ ሱባኤ ይሆናል፤ ፩ዱን ሱባኤ ከ፫ቱ ሱባኤ ሲጨምሩት ፬ት ሱባኤ ይሆናል፤ ፫ት ኢዮቤልዩ ያለው ይህ ነው ፤

ወተፈጸመ መዋዕለ ሕይወቱ ፤

በሕይወት የኖረው ዘመን ተፈ ጸመ ፤

ወልሀቀ አብርሃም ወፈጸመ መዋዕ ሊሁ ፤

አብርሃም አረጀ ዘመኑን ጨረሰ፤

እስመ መዋዕለ ቀደምትሰ እሙንቱ በሕይወቶሙ ፤

የቀደሙ ሰዎች በሕይወት የሚ ኖሩበት ዘመናቸው እነዚህ ናቸው ፤

፲ወ፱ ኢዮቤላውሳት ፤

ዐሥራ ዘጠኝ ኢዮቤልዩ ነበር።

፲፯፤ ወእምድኅረ ማየ አይኅ አንዘ ይንትጉ ዓመታት እም ፲ቱወ፱ ኢዮቤላውስት ፤

ከማየ አይኅ በኋላ ግን ከ፲፱ኙ ኢዮቤላውስት እየጐደለ ይሔድ ጀመር ፤

ወለአሕፅዖ እምኢዮቤላውስት ፤

ከ፲፱ኙ ኢዮቤልዩ በማጉደል፤

ወለረሲዕ ፍጡነ ፤

ፈጥኖ ለማርጀት ፤

ወለተፀግቦ መዋዕሊሆሙ እምገጸ ሕማም ብዙኅ፤

ከብዙ መከራ የተነሣ ዘመና ቸውን በመሰልቸት ፤

በእከየ ፍናዊሆሙ ዘእንበለ አብር ሃም ፤

ከአብርሃም በቀር በሥራቸው ክፋት ፈጥኖ በማርጀት ዘመ ናቸውን ያጐድሉ ጀመር።

፰፤ እስመ አብርሃምሰ ፍጹም በኵሉ ምግባሪሁ ምስለ እግዚአብሔር ፤

አብርሃም ግን ከእግዚአብሔር ጋራ በሚሠራው ሥራ ሁሉ ፍጹም ነበርና ፤

ወእንዘ ያሠምሮ በጽድቅ ኵሉ መዋዕለ ሕይወቱ ፤

ባለ ዘመኑ ሁሉ በውነት እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘት በሚሠራው ሥራ ሁሉ ፍጹም ነበርና፡፡

፱፤ ወናሁ ኢፈጸመ ፩ተ ኢዮቤላ ውስተ በሕይወቱ እስከ አመ ረስዓ ቅድመ ገጸ እከይ ፤

ከመከራ ብዛት የተነሣ ፊጥኖ እስኪያረጅ ድረስ እነሆ አብርሃም በዘመኑ ሁሉ ዐራቱን ኢዮቤልዩ አልጨረሰም፤

ወፀገበ መዋዕሊሁ ፤

አብርሃም ዘመኑን ሰለቸው ፤

ወኵሉ ትውልድ ዘይትነሣእ እምይእዜ እስከ ዕለተ ደይን ዓባይ ይረስዉ ፍጡነ ፤

ከዛሬ ጀምሮ ቁርጥ ፍርድ እስከ ሚፈርድባት ዕለተ ምጽአት ድረስ የሚነሡ ሁሉ ፈጥነው ያረጃሉ ፤

ዘእንበለ ይፈጽሙ ፪ተ ኢዮቤላ ውስተ ፤

ሁለቱን ኢዮቤላውስት ሳይፈጽሙ ያረጃሉ፡፡

፲፤ ወትከውን እንተ ተኀድጎሙ አእምሮቶሙ እምርስዖሙ ፤

ከማርጀታቸው የተነሣ አእምሮአቸው የምትለያቸው ትሆናለች ፤

ወትትአተት ኵላ አእምሮቶሙ ፤

ዕውቀታቸው ሁሉ ፈጽማ ትለያቸዋለች፡፡

፲፩፤ ወበውእቱ መዋዕል እመ ሐይወ ብእሲ ፩ደ ኢዮቤልወ ወመንፈቀ ኢዮቤልዩ ይብሉ በእንቲአሁ አብዝኀ ሐይወ፤

ሰው አንድ አንድ ኢዮቤልዩና የኢዮቤልዩ እኩሌታ ቢኖር ብዙ ዘመን ኖረ ይሉ ነበር፡፡

፲፪፤ ወመብዝኀተ መዋዕሊሁ ሕማም ወሥራህ ወምንዳቤ ፤

ከዚህም በተድላ በደስታ ከሚኖረው በፃዕር በገዐር የሚኖረው ብዙ ነው ፤

ወአልቦ ሰላም ፤

ምንም ምን ተድላ ደስታ የለ ውምና ፤

እስመ መቅሠፍት ዲበ መቅሠፍት፤

በመቅሠፍት ላይ መቅሠፍት፤

ወጽልዓን ዲበ ጽልዓን ፤

በቍስል ላይ ቁስል ፤

ወምንዳቤ ዲበ ምንዳቤ ፤

በመከራ ላይ መከራ ይመጣባቸዋልና ፤

ወስምዓት እኩይ ዲበ ስምዓት እኩይ ፤

በሐሰት ላይ ሐሰት ይመጣባቸዋል ፤

ወደዌ ዲበ ደዌ ፤

በደዌ ላይ ደዌ ይመጣባቸዋል።

፲፫፤ ወኵሉ ኵነኔ እኩይ ዘከማሁ፤

አሁን እንደ ተናገርነው ሁሉ ጽኑ ፍርድ ይመጣባቸዋል ፤

ዝንቱ ኵሉ ኵነኔ ምስለ ዝንቱ ደዌ ፤

ይህ ደዌ ከዚህ መከራ ጋር ይመጣባቸዋል ፤

ወገበጥባጥ ፤

ጓጷ ፤

ወአስሐትያ፤

ውርጭ፤

ወበረድ ፤

በረዶ ፤

ወሐመዳ ፤

ዋግ ፤

ወነበርዓው ፤

ዝንየት ፤

ወሰካህካህ፤

እንቅልፍ ፤

አንድም ግዳጅ፤

ወሰያዛዝ ፤

አእምሮ ማጣት መቅበዝበዝ፤

ወአባር ፤

ድርቅ ፤

ወሞት፤

መቅሠፍት ፤

ወመጥባሕት ፤

የአሕዛብ ሾተል ፤

ወዔዋዌ ፤

ተማርኮ መኼድ ፤

ወኵሉ መቅሠፍት ፤

መቅሠፍቱ ሁሉ ፤

ወሕማም ይከውን ፤

መከራ ይሆናል ይደረጋልና፣

ወኵሉ ዝንቱ ዘይመጽእ በትውልድ እኪት እንተ ትኤብስ ምድረ በርኵሰ ዝሙቶሙ ወበግማኔ ወበ ሰቆራር ግብሮሙ፣

አሁን የተናገርነው መከራ ሁሉ በሚያስጠላ ዝሙታቸው ሀገሩን ሁሉ በምትበድል ትውልድ ይኸ ሁሉ ይመጣል።

ጉባኤ

፲፬፤ ወአሜሃ ይብሉ ለቀደምት መዋዕሊሆሙ ብዙኀ ፤

መከራ በመጣባቸው ጊዜ ከኛ አስቀድሞ የነበሩ አባቶቻችን ዘመናቸው ብዙ ነበር ይላሉ፣

እስከ ፲፻ ዓመት ፤

እስከ ሺህ ዘመን ድረስ ይኖሩ ነበር ፤

ወሠናይ ፤

በተድላ በደስታ ይኖሩ ነበር ይላሉ።

፲፭፤ ወናሁ መዋዕለ ሕይወትነሰ እመ አብዝኃ ሰብአ ሐይወ ፸ ዓመተ ፤

በሕይወት የምንኖረው እኛ ግን ብዙ ዘመን ኖረ ቢባል ፸ ዘመን ነው ፤

ወእመ ኀየለ ፹ ዓመተ ፤

እጅግም ቢበዛ ሰማንያ ዘመን ነው፣

ወኵሉ እኩይ ፤

ከዚህም በመከራ የሚኖረው ይበዛል ፤

ወአልቦ ወኢምንትኒ ሰላም በመዋዕለ ይእቲ ትውልድ እኪት፣

በነዚህ ክፎች ልጆች ዘመን ምንም ምን ተድላ ደስታ የለም።

፲፮፣ ወበይእቲ ትውልድ ይከውኑ ደቂቅ እንዘ ይዘልፉ አበዊሆሙ ወአእሩጊሆሙ ፤

በነዚህ ልጆች ዘመን አባቶቻቸውን ሽማግሎችን የሚሳደቡ ይሆናሉ ፤

በእንተ ኃጢአት ወበእንተ ዓመፃ ፤

በፍጹም ኃጢአታቸው ምክንያት ፤

ወበእንተ ንባበ አፉሆሙ ፤

የማይገባ ነገር በመናገራቸው፤

ወበእንተ እኩያት ግብይት ዘእሙ ንቱ ይገብሩ ፤

እነዚያ በሚሠሩት ጽኑ ኃጢ አታቸው ምክንያት ፤

ወበእንተ ኃዲጎቶሙ ሥርዐተ ዘተ ካየደ እግዚአብሔር ማዕከሌሆሙ ወማዕከሌሁ ፤

እግዚአብሔር በነሳቸውና በሱ መካከል የተማማለውን መሐ ላውን በማፍረሳቸው ምንም ምን ተድላ ደስታ አያገኙም።

፲፯፤ ከመ ይዕቀቡ ወይግበሩ ኵሎ ትእዛዞ ወሥርዐቶ ወኵሎ ሕጎ ፤

ሕጉን ሁሉ ይጠብቁ ዘንድ ትእዛዙን ሥርዐቱን ይሠሩ ዘንድ የተማማለውን መሐላ በማፍረሳቸው፤

ወእልቦሙ ተግኅሦ ፀጋመ ወየማነ፤

ወደቀኝም ወደ ግራም ሁኖ ምንም ምን ማለት የላቸውም በኃጢአት ብቻ የጸኑ ናቸው፤

እስከ ኵሎሙ አእከዩ ፤

ሁሉን ክፉ ሥራ እስከ ማሠራት ድረስ ደርሰው ፤

ወኵሉ አፍ ይትናገር አበሳ ፤

ሰው ሁሉ ኃጢአት የሚሆን ነገርን ይናገራል ፤

ወኵሉ ግብሮሙ ርኩስ ወሰቈራር፤

ሥራቸውም ሁሉ ፈጽሞ የሚ ያጸይፍ ነው ፤

ወኵሉ ፍኖቶሙ ግማኔ ወርኵስ ወሙስና፤

ሥራቸው ሁሉ ፈጽሞ የተ ጠላ የሚጠፋ ነው።

፲፰፤ ናሁ ምድር ትትኃጐል በእንተ ኵሉ ምግባሮሙ ፤

እንሆ በሚሠሩት ኃጢአታቸው ሁሉ ምድር ትጠፋለች ፤

ወአልቦሙ ዘርዐ ወይን ፤

የወይን ዘር ምንም ምን የላቸውም ፤

ወአልቦ ቅብዕ

የሚቀቡት ዘይት የለም ፤

እስመ ኵሉ ካህድ ምግባሪሆሙ ፤

ሥራቸው ሁሉ ክህደት ነውና፤

ወኵሎሙ ይትኃጐሉ ኅቡረ ፤

ሁሉም አንድነት ይጠፋሉ።

፲፱፤ ወይትኃጕሉ አራዊት ወእ ንስሳ ወአዕዋፍ ወኵሉ ዓሣተ ባሕር እምቅድመ ውሉደ ሰብእ ፤

ከሰው ኃጢአት የተነሣ ከሰው ጀምሮ አራዊት እንስሳት አዕዋፍ የባሕር ዓሣት ሁሉ ያልቃሉ ፤

ወይትበአሱ እሉ ምስለ እሉ ፤

አንዱ ከአንዱ ጋራ ይጣላሉ፤

ወራዙት ምስለ ሊቃናት ፤

ሕፃናቱ ከሽማግሎች ጋር ፤

ወሊቃናት ምስለ ሕፃናት ፤

ሽማግሎችም ከሕፃናት ጋር ይጣላሉ ፤

ነዳይ ምስለ ባዕል ፤

ድኃው ከባለጸጋው ጋር ፤

ወትሑት ምስለ ዓቢይ ፤

የተዋረደው ሰው ከከበረው ጋር ይጣላል ፤

ወምስኪን ምስለ መኰንን ፤

ጦም አዳሪው ከሀገረ ገዢው ጋር ይጣላል ፤

በእንተ ሕግ ወበእንተ ኪዳን ፤

መሐላው ሕጉ ስለፈረሰ ይጣላሉ።

፳፤ እስመ ረስዑ ትእዛዘ ወኪዳነ ፤

ትእዛዙን መሐላውን ዘንግተ ዋልና ፤

ወበዓለ ፤

በዓለ መጸለትን ፤ በዓለ ፋሲካን፤ በዓለ ሰዊትን ፤

ወወርኃ ፤

ሠርቀ ወርኅን ፤

ወሰንበተ ፤

ሱባዔውን፤

ወኢዮቤለ፤

፵፱ኙን ዘመን

ወኵሎ ኲነኔ ፤

ሥርዐቱን ሁሉ ዘንግተዋልና፤

ወይቀውሙ በአስይፍት ወበቀትል፤

ሰውን ለመግደል በሰይፋቸው ይጸናሉ ፤

ከመ ይሚጥዎሙ ውስተ ፍኖ ቶሙ መብእስ ፤

ወደክፉ ሥራቸው ይመልሷ ቸው ዘንድ ፤

ወእለ የአቅቡ ሕገ ኢይትመየጡ እስከ ይትከዓው ደም ብዙኀ ውስተ ምድር ፤

ሕጉን የሚጠብቁ ሰዎች በም ድር ብዙ ደም እስኪፈስ ድረስ አይመለሱም ፤

እሉ ዲበ እሉ ፤

እሊህ በሊህ ላይ በጾብ ይነ ሣሉ፤ ትርጓሜው እንዳለፈው ነው ፤

ወእለ ኢድኅኑ በፍኖተ ጽድቅ ኢይትመየጡ እምነ እከዮሙ ለአሕ ዛብ ወይገብሩ እከዮሙ ፤

በውነት ሥራ ያልዳኑ ሰዎች ከክፋታቸው አይመለሱም::

፳፩፤ እስመ ግብሮሙ ትእግልት፤ ሥራቸው ቀሚያ ነውና ፤

ወኵሎሙ ይትነሥኡ ውስተ ብዕል ፤

በገንዘብ ላይ ይነሣሉ ፤

ከመ ይንሣእ ፩ዱ ፩ዱ ኵሎ ዘቢጹ፤

አንዱም አንዱ የባልጀራውን ገንዘብ ይወስድ ዘንድ ሁሉም የሰው ገንዘብ ለመቀማት ይነ ሣሉና ፤

ወስመ ዓቢየ ይሰምዩ ለውሉዶሙ፤

ለልጆቻቸው ታላቅ ስም ያወ ጣሉ ፤

ወአኮ በህልው ፤

ጸንቶ በሚኖር አይደለም ፤

ወአኮ በጽድቅ

በእውነት አይደለም ፤

ወቅድስተ ቅዱሳን ያረኵሱ በርኵሰ ሙስና ግማኔሆሙ ፤

በማይገባ በሥሩት ጥፋትን በሚአመጣ ኃጢአት ከክበሩ የከበረ ቤተ መቅደስን ያረክ ሳሉ::

፳፪፤ ወይከውን መቅሠፍት ዓቢይ ዲበ ግብረ ይእቲ ትውልድ እምኀበ እግዚአብሔር ፤

ከእግዚአብሔር ታዝዞ በዚች ትውልድ ምክንያት ጽኑ መቅ ሠፍት ይሆናል ፤

ወይሁቦሙ ለመጥባሕት ፤

ለሰይፍ አሳልፎ ይሰጣቸዋል፤

ወለኵነኔ

ለቅጣት ፤

ወለዔዋዌ ፤

ለመማረክ ፤

ወለኃይድ ፤

ለመቀማት ፤

ወለብልዓት ፤

ለጥፋት ይሰጣቸዋል ፤

ወያነቅሕ ላዕሌሆሙ ኃጥአኒሆሙ ለአሕዛብ እለ አልቦሙ ልብ ምሕረት ወማህል ፤

ይቅርታ ቸርነት ዕውቀት የሌላቸው የአሕዛብን ወገኖች በነዚያ ላይ ያስነሣባቸዋል።

፳፫፤ ወለገጸ መኑሂ ኢያደልዉ፤

ለማንም ለማን አያዳሉም ፤

ኢ ለልሂቅ ወኢ ለወሬዛ ፤

ለሕፃንም ቢሆን ለሽማግሌም ቢሆን ፤

ወኢለመኑሂ ፤

ለማንም ለማን አያደሉም ፤

እስመ እኩያን ወኃያላን ከመ ይእከዩ እምኵሉ ውሉደ ሰብእ ፤

ከሰው ልጆች ሁሉ ይከፉ ዘንድ ፤

ወይግበሩ በውስተ እስራኤል ሐከከ፤

በእስራኤል ዘንድ ጸብ ክርክር ያደርጉ ዘንድ ክፉዎች ኃይለኞች ናቸውና ፤

ዲበ ያዕቆብ አበሳ ፤

በያዕቆብ ላይ በደልን ያደርጉ ዘንድ ፤

ወይትከዓው ደም ብዙኅ ዲበ ምድር ፤

በምድር ላይ ብዙ ደም ይፈስ ዘንድ ፤

ወአልቦ ዘያስተጋብእ ፤

የሚሰበስብም የለም ፤

ወአልቦ ዘይቀብር፤

የሚቀብርም የለም።

፳፬፤ ወበውእቱ መዋዕል ይጸርሑ ወይጼውኡ ፤

በዝያ ወራት ጮኸው ይጣራሉ፤

ወይጼልዩ ከመ ይድኅኑ እምእደ ኃጥኣን አሕዛብ ፤

ሕገ እግዚአብሔርን ከዘነጉ ከአሕዛብ እጅ ይድኑ ዘንድ ይጸልያሉ ፤

ወአልቦ ዘይሰምዕ ወዘያድኅን ፤

የሚሰማም የሚያድንም የለም፤

ወይፀዐዱ አርእስተ ደቂቅ በሲበት፤

የሕፃናቱ ራስ በሽበት አካለ መጠን ሳያደርሱ ከዓቅመ

አዳም ሳይደርሱ ፈጥነው ይሸ ብታሉ ያረጃሉ ፤

ወያስተርኢ ሕፃን ወልደ ፫ ሱባዔ ልኂቅ ከመ ዘምዕት ዓመቱ ፤

የ፳፩ዱ ዘመን ሕፃን የሶስት ሱባዔ ዘመን ልጅ ፤ የመቶ ዘመን ሽማግሌ መስሎ ይታያል ፤

ወይትነኮል ቀመቶሙ በምንዳቤ ወበፃዕር ፤

ይጐብጥ ሲል ነው ፤ በመከራ በጣር በጋር ይጎብጣሉ፡፡

፳፫፤ ወበውእቱ መዋዕል ይእኅዙ ደቂቅ ይትኃሠሡ ሕገ ፤

በዝያ ወራት ልጆች ሕጉን ይመረምሩ ዘንድ ይጀምራሉ ፤

ወለኃሢሠ ትእዛዝ ወለተመይጦ ውስተ ፍኖተ ጽድቅ ፤

ሥርዓቱን ለመፈለግ ወደ በጎ ሥራ ለመመለስ ይፈልጋሉ ፤

ወይእኅዛ መዋዕል ይብዛሃ ወይ ልሐቃ ፤

ዘመኖችም ፈጽመው ይበዙ ጀመር ፤

ወውሉደ ሰብእ ትውልድ እምት ውልድ ፤

የሰውም ልጅ ከልጅ ልጅ ይበዛ ጀመር ፤

ወዕለት እምዕለት፤

ካንዱ ቀን አንዱ ቀን ይበዛ ጀመር ፤

እስከ ሶበ ይቀርብ መዋዕሊሆሙ ለ፲፻ት ዓመት ፤

ዘመናቸው ወደ ሺህ ዘመን እስኪቀርብ ድረስ፡፡

፳፯፤ ወለብዙኃን ዓመታት እምነ ብዙኀ መዋዕል ፤

ከብዙ ዘመን ተለይቶ ወደ ብዙ ዘመን እስኪደርሱ ድረስ፤

ወአልቦ ልኂቅ ፤

ሽማግሌም የለም ፤

ወአልቦ ዘይፀግብ መዋዕለ ፤

ዘመኑን የሚሰለች የለም ፤

እስመ ኵሎሙ ሕፃናተ ወደቂቀ ይከውኑ ፤

ሁሉም የዓመት የሁለት ዓመት የአርባ የሰማንያ ቀን ልጆች ይሆናሉና ፤

ወኵሎሙ መዋዕሊሆሙ በሰላም ወበፍሥሐ ይፌጽሙ ፤

ዘመናቸውን ሁሉ በደስታ በፍቅር ይፈጽማሉ ፤

ወየሐይዉ በሕይወት ፤

በተድላ በደስታ ይኖራሉ።

፳፯፤ ወአልቦ መኑሂ ሰይጣን ፤

ማንም ማን ባላጋራ የለም ፤

ወአልቦ መኑሂ እኩይ ዘያማስን ሕገ ፤

ሕግን የሚአጠፋ ምንም ምን ክፉ ነገር የለም ፤

እስመ ኵሉን መዋዕሊሆሙ መዋዕለ በረከት ወፈውስ ይከውና፤

ዘመናቸው ሁሉ በረከት ድኅነት የሚገኝበት ዘመን ይሆናልና።

፳፰፤ ወአሜሃ ይፌውስ እግዚአብሔር አግብርቲሁ ፤

ያን ጊዜ እግዚአብሔር ባሮቹ እስራኤልን ያድናቸዋል፤

ወይነሥኡ ወይሬእዩ በዓለም ሰላመ ዓቢየ ፤

በረድኤት ይነሣሉ በዚህ ዓለም ብዙ ደስታ ያያሉ ፤

ወይሰድዱ ጸላእቶሙ ፤

ጠላቶቻቸውን አስወጥተው ይሰዳሉ ፤

ወይሬእዩ ጻድቃን ትፍሥሕተ ወየአኵቱ ፤

ጻድቃን እስራኤል ይህንን አይተው ያመሰግናሉ ፤

ወይትፌሥሑ እስከ ለዓለመ ዓለም በፍሥሐ ፤

ለዘለዓለም በደስታ ይኖራሉ፤

ወይሬእዩ በፀሮሙ ኵሎ ኵነኔሆሙ ፤

በጠላቶቻቸው ላይ የመጣውን መከራ ሁሉ ያያሉ ፤

ወኵሎ መርገሞሙ ፤

ስድባቸውን ሁሉ ያያሉ፤

ወየዓርፍ አዕጽምቲሆሙ ውስተ ምድር ፤

ልጆቻቸውን በዚህ ዓለም ያኖራሉ፤ አንድም አጥንታቸው በመቃብር ይቀበራል ፤

ወመንፈሶሙ ያበዝኅ ትፍሥሕተ፤

ልቡናቸው ደስታውን ያበዛል።

፳፱፤ ወየአምሩ ከመ ሀሎ እግዚ አብሔር ገባሬ ኵሉ ኵነኔ ፤

የሚፈርድ እግዚአብሔር እን ዳለ ያውቃሉ ፤

ወይገብር ሣህለ ወምሕረተ ለአም ዓት ወለአዕላፍ ወለኵሎሙ እለ ያፈቅርዎ ፤

ለሚወዱት ሰዎች ሁሉ ለጥ ቂት ዘመን ለብዙም ዘመን ይቅርታውን ያደርጋል።

፴፤ ወአንተኒ ሙሴ ጸሐፍ ዘንተ ቃለ፤

አንተም ሙሴ! ይኸንን ቃል ጻፈው ፤

እስመ ከመዝ ጽሑፍ ውእቱ ፤

እንዲህ ተጽፏልና ጻፍ አለው መልአክ ገጽ ፤

ወየዓርጉ ውስተ ጽላተ ሰማይ ለትውልድ ዘለዓለም ፤

ለልጅ ልጅ ዘመን ሥርዓት ሊሆን በመላእክት ልቡና ተጻፈ።

## ምዕራፍ ፲፰

፩፤ ወኮነ እምድኅረ ሞተ አብርሃም ባረኮ እግዚአብሔር ለይስሐቅ ወልዱ፤

አብርሃም ከሞተ በኋላ እን ዲህ ሆነ፤ እግዚአብሔር ልጁ ይስሐቅን አከበረው፤

ወተንሥአ ይስሐቅ እምኬብሮን ወሐረ ፤

ይስሐቅም ከኬብሮን ተነሥቶ ሄደ ፤

ወነደረ ኀበ አዘቅተ ራእይ በዓመት አሐዱ ዘሣልስ ሱባዔ ዘዝ ኢዮቤልዩ ሰብዓተ ዓመተ ፤

በዚህ ኢዮቤልዩ በሚቆጠር በሶስተኛው ሱባዔ በአንድ ዓመት ራእይ ከአየበት ዓዘ ቅት ሰባት ዓመት ኖረ።

፪፤ ወበዓመት ፩ዱ ዘሱባዔ ራብዕ አኀዘ አባር ውስተ ምድር ዘእንበለ ቀዳሚ አባር ዘኮነ በመዋዕለ አብርሃም ፤

በአብርሃም ዘመን ከሆነው ከቀደመው ረኃብ ሌላ ባራተ ኛው ሱባዔ በአንድ ዓመት በሀገሩ ሁሉ ረኃብ ሆነ ፤

ወአብሰለ ያዕቆብ ተብሲለ ብርስን፣

ያዕቆብ የምስር ንፍሮ ቀቀለ፣

ወመጽአ ዔሳው እምገቅል ርኁበ፣

ዔሳው ርቦት ከበረሃ መጣ።

፫፤ ወይቤሎ ለያዕቆብ እኁሁ ንበኒ እምዝንቱ ተብሲል ወሥርናይ ፤

ወንድሙን ያዕቆብን ከዚህ ከስንዴው ዳቦ እና ከንፍሮው ስጠኝ አለው ።

፬፤ ወይቤሎ ያዕቆብ አግብእ ሊተ ልህቀተከ ዘቅድመ ልደት ፤

ከመወለድ አስቀድሞ የሆነ ብኵርናህን ስጠኝ አለው ፤

ወአነኒ እሁበከ ኅብስተ ወእምተ ብሲል ፤

እኔም ከምስሩም ንፍሮ ከዳቦ ውም እሰጥሀለሁ አለው።

፭፤ ወይቤ ዔሳው በልቡ እመውት አነ በረሀብ ለምንት ዝቀዲመ ተወልዶ፣

ኤሳውም በልቡ እኔ በረሀብ እሞታለሁ? ከመወለድ የቀደመ ይህ ብኵርና ለምኔ ነው አለ ፤

ወይቤሎ ለያዕቆብ ወሀብኩከ ቀዲመ ተወልዶ ፤

ያዕቆብን ብኵርናዬን ሰጥቸ ሀለሁ አለው።

፮፤ ወይቤ ያዕቆብ መሐል ሊተ ዮም፤

ያዕቆብም አሁን ማልልኝ አለው ፤

ወመሐለ ሎቱ ፤

ማለለት ፤

ወወሀበ ያዕቆብ ኅብስተ ወተብሲለ ለኤሳው እኁሁ ወበልዓ ዔሳው እስከ ይፀግብ ፤

ያዕቆብም ለወንድሙ ዔሳው ዳቦውን ንፍሮውን ሰጠው እስኪጠግብ ድረስ በላ ፤

ወመነነ ዔሳው ቀዲመ ተወልዶ ፤

ኤሳው መጀመሪያ መወለድን ናቀ ፤ ማለት ብኵርናውን አቃለለ።

፯፤ ወበእንተዝ ተሰምየ ስሙ ለኤሳው ኤዶም ፤

ስለዚህ ነገር የኤሳው ስሙ ኤዶም ተባለ፣ ፈታዊ ማለት ነው ፤

በእንተ ተብሲል ወሥርናይ ዘወሀቦ ያዕቆብ ለቅድመ ልደቱ ፤

መጀመርያ ለመወለዱ ያዕቆብ ስንዴውን ንፍሮውን ስለሰ ጠው ፈታዊ (ጉጉ) ተባለ።

፰፤ ወልሕቀ ያዕቆብ ወኤሳውሰ ተትሕተ እምዕበዩ ፤

ያዕቆብ ከበረ ኤሳው ግን ከጌትነቱ ተዋረደ።

፱፤ ወኮነ አባር ዲበ ምድር ፤

በየአገሩ ሁሉ ድርቅ ሆነ ፤

ወመጽአ ይስሐቅ ይረድ ግብፀ በካልዕ ዓመት ዘዝ ሱባዔ ፤

በዚህ ሱባዔ በሁለተኛው ዓመት ይስሐቅ ወደግብፅ ሊወርድ መጣ ፤

ወሖረ ኀበ ንጉሠ ፍልስጥኤም ጌራርሃ ኀበ አቤሜሌክ ፤

ከፍልስጥኤም ንጉሥ ከአቤ ሜሌክ ዘንድ ወደ ጌራሮ ሄደ።

፲፤ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር ለይ ስሐቅ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሔርም ለይስሐቅ ታየው እንዲህም አለው፤

ኢትረድ ግብፀ ንበር ውስተ ምድር እንተ አነ እብለከ ፤

ወደግብፅ አትውረድ እኔ ከአ ልኩህ ቦታ ተቀመጥ እንጂ ፤

ወፍልስ ውስተ ይእቲ ምድር ፤

ወደዚያች አገር ሂድ ፤

ወእሄሉ ምስሌከ ፤

እኔም ካንተ ጋራ በረድኤት ጸንቼ እኖ ራለሁ፤

ወእባርከከ ፤

አከብርሀአለሁ ፤

እስመ ለከ ወለዘርእከ እሁበከ ዛተ ምድረ ኵላ ፤

ይህችን አገር ሁሉ ላንተ ለልጆችህ እሰጥህአለሁና ፤

ወአቀውም መሐላየ ዘመሐልኩ ለአብርሃም አቡከ ፤

ላባትህ አብርሃም የማልኩትን መሐላየን አጸናለሁ፤

ወአበዝኅ ዘርዓከ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ፤

ልጆችህን እንደ ሰማይ ኮከቦች አበዛልሀአለሁ፤

ወእሁብ ለዘርእከ ዛተ ምድረ ኵላ፤

ይህችን አገር ሁላ ለልጆችህ እሰጥአቸዋለሁ።

፲፩፤ ወይትባረኩ በዘርዕከ ኵሎሙ አሕዛበ ምድር ፤

አሕዛብ ሁሉ በልጅህ ይስሐቅ ይከብራሉ፤ አንድም በልጅህ ክርስቶስ ይከብራሉ፤

ህየንተ ሰምዐ አቡከ ቃለ ዚአየ፤

አባትህ የኔን ቃል ስለ ሰማ፤

ወአቀበ ቃልየ ወትእዛዝየ ወሕግየ ወሥርዓትየ ወኪዳንየ ፣

ቃሌን ፣ ትእዛዜን፣ ሕጌን ፣ ሥርዓቴን፣ ቃል ኪዳኔን ፣ ስለ ጠበቀ።

፲፪፤ ወይእዚኒ ስማዕ ቃልየ ወትእዛዝየ፤ አሁንም ቃሌን ትእዛዜን ስማ ፤

ወኅድር ውስተ ዛቲ ምድር ፤

በዚች አገር ኑር፤

ወኀደረ ጌራሮሃ ሠለስተ ሱባዔ ዓመተ ፣

በጌራሮ ሀያ አንድ ዘመን ተቀመጠ ፣

ወአዘዘ አቤሜሌክ በእንቲአሁ ወበእንተ ኵሉ ዘዚአሁ፤

ስለ ገንዘቡ ስለ እሱ ሁሉ አቤሜሌክ አዘዘ፤

እንዘ ይብል ኵሉ ሰብእ ዘይለክፎ ለይስሐቅ ወለኵሉ ዘዚአሁ ሞተ ለይሙት ፤

ገንዘቡን እርሱን ይስሐቅን የሚነካ ሰው ሁሉ ይሙት ብሎ አዘዘ።

፲፫፤ ወልህቀ ይስሐቅ በፍልስ ጥኤም ፣

ይስሐቅ በፍልስጥኤም ኖረ አረጀ፤

ወኮነ ሎቱ ጥሪት ብዙኅ፤

ብዙ ገንዘብ አበጀ ፤

አልሕምት ወአባግዕ አግማል ወአእዱግ ወብዙኅ ጥሪት፤

ብዙ ገንዘብ፣ ብዙ አኽያ፣ ብዙ ግመል፣ ብዙ በግ፣ ብዙ ላም፣ በዙለት ፣

ወዘርዐ ዘርዐ እክል በምድረ ፍልጥኤም ፣

ይስሐቅ ፍልስኤም በሚባል አገር የእህል ዘርን ዘራ።

፲፬፤ ወአዕረገ ምዕተ ሰዊተ ፤

አዲስ እህልን እጽፍ ድርብ አድርጎ መቶ ዳውላ አገባ ፤

ወዐብየ ይስሐቅ ፈድፋደ ፤

ይስሐቅ ፈጽሞ ከበረ ገነነ ፤

ወቀንዑ ሳዕሌሁ ፍልጥኤም ፤

የፍልስጥኤም ሰዎች በላዩ ላይ ቀኑበት ተነሱበት ፤

ወኵሎ ዓዘቃተ ዘከረዩ ደቀ አብርሃም በሕይወተ አብርሃም ደፈኑ፤

አብርሃም በሕይወተ ሥጋ ሳለ ልጆቹ የቆፈሩትን የውሀ ውን ጉድጓድ ደፈኑ ፤

እምድኅረ ሞተ አብርሃም ፤

አብርሃም ከሞተ በኋላ የፍል ስጥኤም ሰዎች ፤

ወመልእዎን መሬተ፤

አፈር መልተው ደፈኑት።

፲፭፤ ወይቤሎ አቤሜሌክ ለይስ ሐቅ ሑር እምኀቤነ፤

አቤሜሌክ ይስሕቅን ከሀገራ ችን ተነሥተህ ሂድ አለው፤

እስመ ዓበይከ ፈድፋደ እምኔነ ፤

ከኛ አንተ እጅግ ከብረሀል ገነሀልና።

፲፮፤ ወሖረ ይስሐቅ በ፩ ዓመት ዘሱባዔ ሳብዕ እምሀየ ወፈለሠ ውስተ ቈላተ ጌራሮን ፤

በሰባተኛው ሱባዔ በአንደኛው ዓመት ይስሐቅ ወደ ጌራራ ቆላ ተነሥቶ ሄደ።

፲፯፤ ወተመይጠሙ ከረዩ አዘ ቃተ ዘማያት ዘከረዩ ደቀ አብርሃም አቡሁ ፤

ተመልሰው የአባቱ የአብር ሃም ብላቴኖች የቆፈሩትን የውሀውን ጉድጓድ ከፈቱ ፤

ዘደፈንዎ ፍልስጥኤም እምድኅረ ሞተ አብርሃም አቡሁ ፤

አባቱ አብርሃም ከሞተ በኋላ የፍልስጥኤም ሰዎች ደፍነ ውት የነበረውን የውሀ ጉድጓድ መልሰው ቆፍረው ከፈቱት፤

ወጸውአን አስማቲሆን ዘሰመዮን አብርሃም አቡሁ ፤

ስማቸውን አባቱ አብርሃም በጠራቸው ስም ጠራቸው ፤

ወከረዩ ደቀ ይስሐቅ አዘቃተ በፋንጋ ፤

የይስሐቅ ብላቴኖች የውሀ ውን ጉድጓድ በፋንጋ ቆፈሩ፤

ወረከቡ ማየ ሕያወ ፤

የጠራ ውሀን አገኙ።

፲፰፤ ወተገአዙ ኖሎተ ጌራሮን ምስለ ኖሎተ ይስሐቅ እንዘ ይብሉ ዘዚአነ ዝንቱ ማይ ፤

የጌራሮን እረኞች ከይስሐቅ እረኞች ጋር ይኸ ውሀ የኛ ነው እያሉ ተጣሉ ፤

ወጸውኦ ይስሐቅ ስሞ ለውእቱ ዓዘቅት ዕፁብ ፤

ይስሐቅ የዚያን የውሀ ጉድ ጓድ ስሙን ጭንቅ አለው፤

እስመ ተፃብዑ ምስሌነ ፤

ከኛ ጋራ ተጣልተዋልና ብሎ፤

ወከረዩ ዓዘቅተ ካልዐ ፤

ሌላ ጉድጓድን ቆፈሩ ፤ ወተበዓሉ በእንቲአሁኒ፤

በዚያም ተጣሉ ፤

ወጸውአ ስሞ ጸባብ ፤

ስሙን ጠብ የተደረገበት አለው።

፲፱፤ ወተንሥአ ይስሐቅ እምህየ፤

ይስሐቅም ከዚያ ተነሥቶ ሄደ፤

ወከረዩ ዓዘቃተ ካልዓነ ወኢተበአሱ በእንቲአሁ ፤

ሌላ የውሀ ጉድጓድን ቆፈሩ ስለዚህ ግን አልተጣሉም፤

ወጸውአ ስሞ ስፋሕ ፤

ስሙን ሰፊ አለው።

፳፤ ወይቤ ይስሐቅ ይእዜ አስፍሐ ለነ እግዚአብሔር ፤

ይስሐቅም ዛሬ እግዚአብሔር አገር አሰፋልን አለ፤

ወልህቅነ ዲበ ምድር ፤

በምድር ላይ ከበርን ፤

ወዐርገ እምህየ ውስተ ዓዘቅተ መሐላ፤

ከዚያ ተነሥቶ ወደቤርሳቤህ ሄደ፤

በቀዳሚ ዓመት ዘሱባዔ ቀዳሚ በ፵ወ፩ዱ ኢዮቤልዩ ፤

በመጀመርያው ዓመት በመጀመርያው ሱባዔ፤ ባርባ አንደኛው ኢዮቤልዩ ወደቤርሳቤህ ወጣ።

፳፩፤ ወአስተርአዮ እግዚአብሔር በይእቲ ሌሊት በሠርቀ ቀዳሚ ወርኅ ፤

በመጀመርያው ወር በሚያዝያ በዚች ሌሊት እግዚአብሔር ታየው ተነጋገረው፤

ወይቤሎ አነ ውእቱ አምላከ አብርሃም አቡከ ኢትፍራህ ወኢትደንግጽ፤

የአባትህ የአብርሃም ፈጣሪ እኔ ነኝና አትፍራ አትደንግጥ አለው ፤

እስመ አነ ሀሎኩ ምስሌከ ፤

እኔ ካንተ ጋራ በረድኤት ጸንቼ እኖራለሁና ፤

ወእባርከከ ወአበዝኆ አበዝኆ ዘርዓከ ፤

አከብርሃለሁ ዘርህን እንደ ባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ፤

ወከመ ኆፃ ባሕር በእንተ አብርሃም ቍልዔየ ፤

ስለ ወዳጄ አብርሃም ልጅህን እንደባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ አለው።

፳፪፤ ወሐነፀ ይስሐቅ ህየ ምሥዋዐ ዘቀዳሚ ሐነፀ አብርሃም አቡሁ ፤

አባቱ አብርሃም ቀድሞ በሠራው መሠዊያ ላይ ደግሞ መሠዊያን ሠራ ፤

ወጸውአ ስመ እግዚአብሔር ፤

የእግዚአብሔርን ስም ጠራ ፤

ወሦዐ መሥዋዕተ ለአምላከ አብርሃም አቡሁ ፤

ለአባቱ አብርሃም ፈጣሪ መሥዋዕትን ሠዋ፤

ከረዩ ዓዘቅተ ወረከበ ማየ ሕያወ ፤

የውሃ ጉድጓድን ቆፍሮ ጥሩ ውሀን አገኘ።

፳፫፤ ወደቀ ይስሐቅኒ ከረዩ ዓዘቅተ ካልዓ ወኢረከቡ ማየ ፤

የይስሐቅ ብላቴኖች ሌላ ጉድጓድ ቆፍረው ውሀ አላገኙም፤

ወሖሩ ወነገርዎ ለይስሐቅ ከመ ኢረከቡ ማየ፤

ውሀ እንዳላገኙ ለይስሐቅ ነገሩት።

፳፬፤ ወይቤ ይስሐቅ መሐልኩ በዛቲ ዕለት ለፍልስጥኤም ፤

ይስሐቅም በዚች ቀን ለፍልስ ጥኤም ሰዎች በግድ ማልኩ አለ፤

ወኮነ ለነ ዝንቱ ነገር ፤

በግድ መማላችን ለኛ በጎ ነገር ሆነልን፤

ወጸውአ ስሞ ለውእቱ መካን ዓዘቅተ መሐላ፤

ያነን ቦታ ስሙን ዓዘቅተ መሐላ ፤ መሐላ የተደረገበት ጕድጓድ አለው ፤

እስመ በህየ መሐለ ለአቤሜሌክ ፤

በዚያች ቀን ለአቤሜሌክ ምሎ አልና ፤

ወለአኮዘት ካልዑ ሎቱ ፤

ለሁለተኛው ለአኮዘት ወዳጁ ማለለት ፤

ወለፋኮል ፀቃቢሁ ፤

ለጠባቂው ፋኮልም ማለለት።

፳፭፤ ወአእመረ ይስሐቅ በይእቲ ዕለት ከመ በግፍዕ መሐለ ሎሙ ለገቢር ምስሌሆሙ ሰላመ ፤

ይስሐቅም ከነዚያ ጋራ ፍቅር አድነትን ለማድረግ በዝያች ቀን በግፍዕ በማይገባ እንደ ማለላቸው አወቀ ፤

ወረገሞሙ ይስሐቅ በይእቲ ዕለት ለፍልስጥኤም ፤

ይስሐቅ በዝያች ቀን የፍልስ ጥኤምን ሰዎች ረገማቸው ፤

ወይቤ ርጉም ፍልስጥኤም በዕለተ መዓት ወቍጥዓ ፤

ቍጣ ፍርድ በሚደረግበት ቀን የፍልስጥኤም ሰው ርጉም ነው፤

እማዕከለ ኵሉ አሕዛብ ፡ የሀቦ እግዚአብሔር ለዝንጓጒ ወለመርገም ወለመዓት ፤

በሕዝቡ ሁሉ መካከል እግዚ አብሔር ለሽሙጥ ለመርገም ለመዓት ይስጠው ፤

ወቍጥዓ በእደ ኃጥአን አሕዛብ ፤

ኃጥአን በሆኑ በአሕዛብ እጅ ይጣላቸው ፤

ወውስተ እደ ኬጤኤም ይሥር ውምሙ፤

በሮማውያንም እጅ ይጣላ ቸው፤ አንድም ይሠርውምሙ፤ መላእክት ሥላሴ በኬጤኤም እጅ ጥለው ያጥፏቸው።

፳፯፤ ወዘአምሠጠ እምሰይፈ ፀር፤

ከጠላት ሰይፍ ያመለጠውን፤

ወእምነ ኬጤኤም ፤

ከሮም ጦርም ያመለጠውን ፤

ይሥርውምሙ ሕዝብ ጻድቃን በኵነኔ እምታሕተ ሰማይ ፤

ደጋጎች ወገኖች ከሰማይ በታች በዚህ ዓለም በመከራ ያጥፏ ቸው፤

እስመ ፀረ ወጸላእተ ይከውኑ ለውሉድየ በመዋዕሊሆሙ በዲበ ምድር ፤

በዚህ ዓለም በዘመናቸው ለል ጆቼ የዕለት ጠላት ጥንተ ጠላት ይሆኗቸዋልና።

፳፯፤ ወአልቦ ተኀድጎ ሎሙ ተረፍ ፤

ልጅ የልጅ ልጅ የላቸውም ፤

ወአልቦ ዘይድኀን አመ ዕለተ ኵነኔ መዓት ፤

ፍርድ በሚፈረድበት ቀን የሚ ድን የለም ፤

እስመ ለኃጕል ወለሥራዌ ወለሰ ስሉ እምነ ምድር ኵሉ ዘርዐ ፍልስጥኤም ፤

የፍልስጥኤም ልጅ ሁሉ ከዚህ ዓለም ለመራቅ ለመነቀል ለጥ ፋት ተዘጋጅቷልና።

፳፰፤ ወአልቦ እንከ ለኵሉ ከፍቱር ምንትኒ ስም ዘተርፈ ፤

ባልተገረዘ ሰው የሚነገር ምንም ስም የለም ፤

ወዘርዕ ላዕለ ምድር ፤

በምድር ላይ የሚኖር ልጅ የለም ፤

እስመ እመኒ እስከ ሰማይ የዐርግ እምህየ ይወርድ ፤

ምንም እስከ ሰማይ ቢወጣ ከዚያ ይወርዳልና ፤

ወእመኒ ፀንዐ ውስተ ምድር እምህየ ይትመላህ ፤

በምድርም ቢፀና ከዚያ ይጠፋል ፤

ወእመኒ ተኃብአ ማእከለ አሕዛብ እምህየኒ ይሤሮ ፤

በአሕዛብም መካከል ቢሰወር ከዚያ ይጠፋል።

፳፱፤ ወእመኒ ወረደ ውስተ ሲኦል በህየኒ ይበዝኅ ኵነኔሁ ፤

ወደሲኦልም ቢወርድ በዚያ መከራ ይፀናበታል ፤

ወአልቦ ሎቱ በህየ ምንትኒ ሰላም፤

በዚያም ምንም ምን ተድላ ደስታ የለውም።

፴፤ ወእመኒ ሖረ ውስተ ዔዋዌ በእደ እለ የሐሥሥዋ ለነፍሱ በማዕከለ ፍኖት ይቀትልዎ ፤

ሰውነቱን ለጥፋት በሚፈልጉት እጅ ተማርኮ ቢሔድ በጎዳና መካከል ይገሉታል ፤

ወአልቦ አትርፎ ሎቱ ስም ወዘርእ ውስተ ኵሉ ምድር ፤

በዚህ ዓለም ስም ልጅ የሚቀርለት የለም ፤

እስመ ውስተ መርገም ዘለዓለም የሐውር ፤

ለዘለዓለም ወደሚኖር መከራ ይሔዳልና።

፴፩፤ ወከመዝ ተጽሕፈ ወተቀርፀ በእንቲአሁ ውስተ ጽላተ ሰማይ ለገቢር ሎቱ በዕለተ ኵነኔ ከመ ይሠረው እምድር ፤

ከዚህ ዓለም ይጠፋ ዘንድ በሚፈረድበት ቀን ለማድረግ ስለ እሱ በመላእክት ልቡና እንዲህ ተጽፏል ታውቋል።

## ምዕራፍ ፲፱

### ጉባኤ

፩፤ ወበካልዕ ዓመት ዘዝ ሱባዔ በዝ ኢዮቤልዩ ፀውዐት ርብቃ ያዕቆብሃ ወልዳ ፤

በዚህ ሱባዔ በሁለተኛው ዓመት በዚህ ኢዮቤልዩ ርብቃ ልጇ ያዕቆብን ጠራች፤

ወተናገሬቶ እንዘ ትብል ወልድየ ኢትንሣእ ለከ ብእሲተ እምአዋልደ ከነአን ፤

እንዲህም ብላ ተናገረችው ልጄ ከከነአን ልጆች ወገን ሚስት አታግባ ፤

ከመ ኤሳው እትከ ዘነሥአ ሎቱ ብእሲተ ፪ኤተ አምዘርዓ ከነአን፤

ከከነአን ልጆች ሁለት ሴቶ ችን እንዳገባ እንደወንድምህ ኤሳው ፤

ወአምረራሃ ለነፍስየ በኵሉ ምግባ ሮን ርኵስ ፣

በክፉ በማይገባ ሥራቸው ሰውነቴን አሳዘኗት ፣

እስመ ኵሉ ምግባሮን ዝሙት ወምርዓት ፣

ሥራቸው ሁሉ ዝሙት መዳ ራት ዋዛ ፈዛዛ ነውና ፤

ወአልቦ ምንትኒ ጽድቅ ምስሌሆን፤

ከነሳቸው ዘንድ ምንም ምን እውነት ነገር የለም ፣

እስመ እኩይ ውእቱ ግብሮን ፤

ሥራቸው ክፉ ነውና፤

፳፤ ወአነ ኦ ወልድየ አፈቅረከ ጥቀ ፈድፋደ ፣

ልጄ ሆይ ! እኔ እጅግ አብ ዝቼ እወድሀለሁ ፤

ወልብየ ወምሕረትየ ይባርከክ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ዕለት ፣

በየጊዜው በየቀኑ ሁሉ ልቡ ናየ ይቅርታየ ያከብርሃል፤

ወዑቃቤ ለያልይ ፣

የሌሊት መልአክ ዑቃቤየ ያከ ብርሃል ፤ ይጠብቅሃል ይመ ርቅሃል አለችው፤

፳፩፤ ወይእዜኒ ወልድየ ስማዕ ቃልየ፤

አሁንም ልጄ ነገሬን ስማ ፣

ወግበር ፈቃዳ ለእምከ ፣

የናትህን ፈቃድ አድርግ ፣

ወኢትንሣእ ለከ ብእሲተ እምአዋ ልደ ዝ ምድር ፤

ከዚህ ሀገር ልጆች ሚስት አታግባ ፣

ዘእንበለ እምቤተ አቡከ ፤

የምታገባትን ሚስት ከአባቴ ወገን አግባ እንጂ ፣

ወይባርከከ አምላክ ልዑል ፣

ገናና አምላክ ያከብርሃል ፤

ወይከውኑ ውሉድከ ትውልደ ጽድቅ ፤

ልጆችህም የእውነት ልጆች ይሆናሉ ፤

ወዘርዕከ ይከውን ቅዱስ ፤

ልጅህም ክቡር ይሆናል።

፬፤ ወእምዝ ተናገረ ያዕቆብ ምስለ ርብቃ እሙ፤

ከዚህም በኋላ ያዕቆብ ከናቱ ከርብቃ ጋራ ተነጋገረ ፤

ወይቤላ ናሁ እምየ አነ ወልደ ፱ቱ ሱባዔ ዓመት ፤

እናቴ እነሆ እኔ የዘጠኝ ሱባዔ ዘመን ልጅ ነኝ ፤

ወኢምንተኒ አንስተ ኢየአምር ፤

ምንም ምን ሴት አላውቅም፤

ወኢገሠሥኩ ፤

የሴት እጅ አልጨበጥኩም ፤

ወኢኃፈርኩ ፤

ኢኃሠሥኩ ሲል ነው፤ አንድም ኢፈኀርኩ ይላል አላጨሁም፤

ወኢይሄሊ እንከ እንሣእ ብእሲተ እምኵሉ ዘርአ አዋልደ ከነአን ሲተ፤

ከከነአን ሴቶች ወገን ሚስት አገባ ዘንድ አላስብም ፤

እስመ እዜከር አነ እምነገረ አብርሃም ኣቡነ ፤

ከአባታችን አብርሃም ነገር የተነሣ እኔ አስብአለሁና ፤

ምንተኒ ዘአዘዞኒ ከመ ኢይንሣእ ብእሲተ እምኵሉ ዘርዐ ቤተ ከነአን፤

ከከነአን ወገኖች ልጆች ሁሉ ምንም ምን ሚስት እንዳላገባ ያዘዘኝን አስብአለሁና፤

እስመ እምዘርዐ ቤተ አቡየ እነሥእ ሊተ ብእሲተ ፤

እኔ ካባቴ ወገን ሚስት አገባለሁ እንጅ ።

፭፤ ሰማዕኩ እምቀዲሙ ከመ ተወልዳ እዋልድ ለላባ እትኪ ፤

ለወንድምሽ ለላባ ሴቶች ልጆች እንደተወለዱ ከዘመዶቼ ወገን አስቀድሜ ሰማሁ ፤

ወበላዕሌሆን አንበርኩ ልብየ ከመ እምኔሆን እንሣእ ብእሲተ ፤

ከነዚያ ሚስትን አገባ ዘንድ ልቡናየን በነሱ ላይ አስቀ መጥሁ አሳረፍኩ።

፯፤ ወበእንተዝ አነ ተአቀብኩ በመንፈስየ ከመ ኢየአብስ፤

ስለዚህ ነገር እንዳልበድል እኔ በሰውነቴ ተጠበቅሁ ፣

ወኢያማስን በኵሉ ፍናውየ ኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ ፤

በምሠራው ሥራ ሁሉ አኗኗሬ እንዳይጠፋ ፤

እስመ በእንተ ምርዓት ወዝሙት አብዝኀ አቡየ አብርሃም አዝዞትየ፤

የዝሙትን የዋዛን የፈዛዘን ነገር እንዳላደርግ አባቴ አብርሃም አብዝቶ አዘኛልና፣

ወምስለ ኵሉ አዘዘኒ ዘንተ ፤

ከዚህም ሁሉ ጋራ ይኸን በጽኑ አዘዘኝ ፣

፳ወ፪ ዓመት እትየ ኤሳው እንዘ ይትገአዘኒ ፤

ወንድሜ ኤሳው ሲከራከረኝ ሀያ ሁለት ዘመን ነው፤

ወያበዝኀ እንዘ ይትናገረኒ ፣

አብዝቶ ሲዘበዝበኝ፤

ወይብል ንሣእ እትየ ብእሲተ እሐተ እኀቶን ለእንስትያየ ፪ቲ ፣

ከ፪ቱ ሚስቶቼ እኅቶች አንዷን አግባ ብሎ (እያለ)።

፰፤ ወአነኒ ኢይፈቅድ እግበር ከመ ገብረ እትየ ፤

እኔ ግን ወንድሜ እንዳደረገው አደርግ ዘንድ አልወድም ፤

ወእምሕል አነ እምቅድሜኪ ኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ ከመ ኢይነሥእ ሊተ ብእሲተ እምኵሉ ዘርዐ አዋልደ ከነአን ፤

ከከነአን ልጆች ወገን ሁሉ እኔ ሚስት እንዳላገባ ባለ በዘመኔ ሁሉ በፊትሽ እምላለሁ ፤

ወኢየአኪ ገቢረ በከመ ገብረ እትየ፤

ወንድሜ ክፉ ነገር እንዳደረገ አላደርግም፤

ኢትፍርሂ እምየ ፤

እናቴ አትፍሪ፤

ተአመኒ ከመ እገብር ፈቃደኪ፤
ፈቃድሽን እንዳደርግ እመኚ

ወበርቱዕ አሐውር ፤

በቀና ነገር ጸንቼ እንድኖር እመኚ ፤

ወኢያማስን ፍናውየ ለዓለም ፤

ሥራየን ለዘላለሙ እንዳላጠፋ እመኚ አላት።

፳፤ ወእምዝ አንሥአት ገጸ ውስተ ሰማይ፤

ከዚህ በኋላ ፊቷን ወደ ሰማይ አቀናች ፤

ወሰፍሐት አፃብአ እደዊሃ ፤

እጆቿን ወደሰማይ ዘረጋች፤

ወከሠተት አፋሃ ፤

አፏን ገለጠች ማለት ነገር ጀመረች ፤

ወባረከቶ ለአምላክ ልዑል ዘፈጠረ ሰማየ ወምድረ ፤

ሰማይን ምድርን የፈጠረ ገናና አምላክን አመሰገነችው ፤

ወወሀበት ሎቱ አኰቴተ ወስባሔ፤

ምስጋናን ክብርን አቀረበች።

፱፤ ወትቤ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኪየ ፤

ፈጣሪየ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን አለች ፤

ወይትባረክ ስሙ ለዓለመ ዓለም ዘወሀበኒ ያዕቆብሃ ወልደ ንጹሐ ወዘርዐ ቅዱሰ ፤

ክቡር ዘርዕ ንጹሕ ልጅ ያዕቆብን የሰጠኝ ፈጣሪየ ስሙ ለዘለዓለም ይክበር ይመስገን አለች ፤

እስመ ዚአከ ውእቱ

እሱ ያንተ ገንዘብ ነውና ፤

ወለከ ይኩን ዘርዑ ውስተ ኵሉ መዋዕል በኵሉ ትውልድ ዘለ ዓለም፤

ለዘለዓለም በሚኖር ትውልድ ሁሉ እስከ ብዙ ዘመን ድረስ ላንተ ልጅ ተገዥ ይሁን።

፲፤ ባርኮ እግዚኦ አምላኪየ ለያዕቆብ ወልድየ ፤

አቤቱ! ፈጣሪዬ ልጄ ያዕቆብን አክብረው ፤

ወአንብር ውስተ አፋየ በረከተ ጽድቅ ከመ እባርኮ፤

እመርቀው ዘንድ ትንቢትን የሚያናግር መንፈስ ቅዱስን ባንደበቱ አኑርልኝ።

፲፭፤ ወውእተ ጊዜ ወረደ መንፈስ ቅዱስ ውስተ አፉሃ ፤

ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ባንደበቷ ተሳለ እናገራት ፤

ወአንበረት ውስተ ርእሰ ያዕቆብ ፪ኤሆን አእዳዊሃ ፤

ሁለቱን እጆቿን በያዕቆብ ራስ ላይ አኖረች ፤

ወትቤ ቡሩክ አንተ እግዚአ ጽድቅ፤

የእውነት ጌታ አንተ ክቡር ነህ ምስጉን ነህ አለች፤

ወአምላከሙ ለዓለማት፤

የመላእክት የጻድቃን ፈጣሪ።

፲፱፤ ወኪያከ ይባርክ እምኵሉ ትውልደ ሰብእ ፤

ከሰው ልጅ ሁሉ ለይቶ አንተን ያክብር ፤

የሀብከ ወልድየ ፍኖተ ጽድቅ ፤

ልጄ ! እውነተኛውን ሥራ ይስጥህ ፤

ወለዘርዕከ ይክሥት ጽድቀ ፤

ለልጅህም እውነትን ነገር ይግ ለፅለት ፤

ወያብዝኅ ውሉደከ በሕይወት ፤

በሕይወት ሳለህ ልጆችህን ያብዛልህ፤

ወይቁሙ በኍልቄ አውራኅ ዓመት

አንዱ ዘመን ወደ አንዱ ዘመን በሚመላለስበት ወራት ጸንተው ይኑሩ ፤ አንድም በአ ሥራ ሁለቱ ወሮች ቁጥር አሥራ ሁለት ልጆች ይወለ ዱልህ ፤

ወውሉዶሙ ይብዝኍ ወይዕበዩ እምነ ከዋክብተ ሰማይ ፤

ልጆቻቸውም ከሰማይ ከዋክ ብት ይብዙ ይብለጡ ፤

ወእምነ ኆፃ ዘባሕር ይብዛኅ ኍልቆሙ ፤

ቍጥራቸውም ከባሕር አሸዋ ይብዛ ፤

ወየሀቦሙ ዛተ ምድረ ሠምርተ በከመ ነበበ የሀቦ እግዚአብሔር ለአብርሃም ወለዘርዑ እምድኅሬሁ በኵሉ መዋዕል ፤

እግዚአብሔር ለአብርሃም ከሱም በኋላ ለልጆቹ ባለ ዘመኑ ሁሉ ይሰጠው ዘንድ እንደተናገረ ይህችን ያማረች የተወደደች አገር ይስጣቸው።

፲፫፤ ወየአኀዝዋ እጊዘ ዘለዓለም፤

ለዘለዓለም እጅ አድርገው ይያዟት ፤

ወእርአይ ለከ ወልድየ ወልደ ቡሩከ በሕይወትየ ፤

ልጄ! በሕይወት ሳለሁ ደግ ልጅ ተወልዶልህ ልይ ፤

ወዘርአ ቅዱስ ወቡሩከ ይኩን ኵሉ ዘርዕከ ፤

ልጅህ ሁሉ የከበረ የተባረከ ይሁን ፤

ወበከመ አዕረፍከ መንፈሰ እምከ በሕይወታ ፤

በሕይወት ሳለች የናትህን ልቡና እንዳሳረፍከ ፤

ከርሣ ለወላዲትከ ፤

ማኅፀና ሲል ነው ፤

ከመዝ ትባርከ ፤

የናትህ ማኅፀኗ እንዲህ እንዲሁ ታክብርህ ፤

ምሕረትየ ወአጥባትየ ኪያከ ይባርኩ፤

ይቅርታየ ጡቶቼ አንተን ያክብሩ ፤

ወአፉየ ወልሳንየ ኪያከ ያእኵቱ ፤

አፌ አንደበቴ አንተን ያመስግኑ ፤

ብዛኀ ወለሐቅ ወተከዐው ውስተ ምድር ፤

የብዙ ብዙ ሁን በዓለም ሁሉ ምላ ፤

ወዘርዕከ ይኩን ፍጹመ ውስተ ኵሉ ዓለም በፍሥሐ ሰማይ ወምድር ፤

በስፍሐ ሰማይ ሲል ነው፤ በምድርና በሰማይ ስፋት በዓለም ሁሉ ልጅህ ፍጹም ይሆን ዘንድ፤ አንድም በሰማይ በምድር በሚደረግ ተድላ ደስታ ፍጹም ይሁን፤

ወይትሐሠይ ዘርዕከ ፤

ልጅህ ደስ ይበለው።

፲፬፤ ወበዕለተ ሰላም ዓባይ ይኩን ሎቱ ሰላም ፤

ብዙ ተድላ ደስታ በሚደረግ በት ቀን ተድላ ደስታ ፍቅር ይደረግለት፤

ስምከ ወዘርዕከ እስከ ኵሉ ዓለማት ይቁም ፤

ስምህ ልጅህ እስከ ብዙ ዘመን ድረስ ጸንቶ ይኑር ፡

ወአምላክ ልዑል ሎሙ አምላክ ፡

ገናና ፈጣሪም ጠባቂ ይሁና ቸው ፤

ወአምላከ ጽድቅ ምስሌሆሙ ይኅድር ፤

እውነተኛ ፈጣሪ ከነሳቸው ጋራ በረድኤት ጸንቶ ይኑር፤

ወቦሙ ይትሐነጽ መቅደሉ ውስተ ኵሉ ዓለማት ፤

በዓለሙ ሁሉ ደብተራ ኦሪት፣ ቤተ መቅደስ ፣ ቤተ ክርስቲያን በነሱ ይሠራ ይታነጽ፤

ወዘይባርከከ ይኩን ቡሩከ ፤

የሚመርቅህ ሰው የተመረቀ ይሁን ፤

ወኵላ ሥጋ እንተ ትረግመከ በሐሰት ትኩን ርግምተ ፤

በሐሰት አንተን የምትረግምህ ሰውነት ሁሉ የተረገመች ትሁን አለች።

፲፰፤ ወሰዐመቶ ለወልዳ፤

ልጇን ሳመችው ፤

ወትቤሎ ያፍቅር ብከ እግዚእ ለዓለም በከመ ልበ እምከ፣

የናትህ ልቡና እንደሚወድህ አንተን ጌታ ለዘለዓለሙ ይውደድህ አለችው ፤

ወምሕረታ ይትሐሠይ ብከ ወይባርከከ ፤

ይቅርታዋ በአንተ ደስ ይበለው ያክብርህ ይመርቅህ፣

ወአርመመት እንከ እምባርኮ ፤

ትንቢት ከመናገር ከመመረቅ ዝም አለች።

፲፱፤ ወበዓመት ሳብዕ ዘዝሱባዔ ፀውዐ ይስሐቅ ኤሳውሃ ወልዶ ዘይልኅቅ ፤

በሰባተኛው ዓመት በዚህ ሱባዔ ታላቅ ልጁ ኤሳውን ይስሐቅ ጠራው፤

ወይቤሎ ወልድየ አነ ረሳእኩ፤

ልጄ ! እኔ አረጀሁ አለው፣

ወናሁ አዕይንትየ ከፍአ ለርእይ ፣

እንሆ አይኖቼ ለማየት ፈዘዙ፤

ወኢየአምር ዕለተ ሞትየ፤

የምሞትበትን ቀን አላውቀውም።

፲፯፤ ወይእዜኒ ንሣእ ንዋየ ነዓዊከ ወምጕንጳከ ወቀስተከ ወዓዕሐቅለ ፤

አሁንም ጦርህን ቀስትህን የአደን መሣርያህን ይዘህ ወደ ምድረ በዳ ሂድ ፤

ወነዓው ሊተ ፤

አድንልኝ ፤

ወአሥግር ወአኃዝ ሊተ ወልድየ፤

ልጄ አጥምደህ አድነህ አምጣልኝ።

ወግበር ሊተ መብልዐ ከመ ዘታፈቅር ነፍስየ ፤

ልቡናየ እንደምትወደው ምግቡን አዘጋጅተህ ፤

አምጽእ ሊተ ከመ እብላእ ፤

እበላ ዘንድ አምጣልኝ ፤

ወትባርከ ነፍስየ ዘእንበለ እሙት፤

ሳልሞት ሰውነቴ ትመርቅህ ዘንድ አለው ፤

ወርብቃሰ ትሰምዕ ነገሮ እንዘ ይነግሮ ይስሐቅ ለኤሳው፤

ርብቃ ግን ይስሐቅ ለኤሳው ነገሩን ሲነግረው ትሰማ ነበር፤

፲፰፤ ወጌሠ ኤሳው ገዳመ ከመ ያሥግር ወየአኃዝ ከመ ያምጽእ ለአቡሁ ፤

ኤሳው ወደ ምድረ በዳ ሄደ አጥምዶ አድኖ ይዞ ላባቱ ያመጣለት ዘንድ።

፲፱፤ ወጸውዐት ርብቃ ያዕቆብሃ ወልዳ ፤

ርብቃም ልጇ ያዕቆብን ጠራች፤

ወትቤሎ ናሁ ሰማዕክዎ

ለይስሐቅ አቡከ እንዘ

ይትናገር ምስለ ኤሳው እኁከ ፤

ከወንድምህ ከኤሳው ጋራ ሲናገር አባትህ ይስሐቅን እንሆ ሰማሁት አለችው፤

እንዘ ይብል አሥግር ሊተ ወግበር ሊተ መብልዐ፤

አድነህ አምጥተህ መብሉን አዘጋጅልኝ ፤

ወአብስል ሊተ ወእብላእ ፤

አብስለህ አምጣልኝ ልብላ፤

ወእባርከ በቅድመ እግዚአብሔር ዘእንበለ እሙት ፤

ሳልሞት በእግዚአብሔር ፊት እመርቅህ ዘንድ ፤

፳፤ ወይእዜኒኬ ስማዕ ቃልየ ዘአነ እኤዝዘከ ወልድየ ፤

ልጄ ! እኔ የማዝህን ቃል ስማኝ ፤

ሑር ውስተ መርዔትከ ፤

ወደመንጋህ ሂደህ ወንሣእ ሊተ ፪ተ መሐስዓ ጠሊ ሠናያነ ፤

ያማሩ የወፈሩ ፪ት የፍየል ጠቦቶች አምጣልኝ አለችው፤

ወእግበሮሙ መብልዐ ለአቡከ ዘከመ ያፈቅር ፤

እንደሚወደው አድርጌ ምግቡን ላባትህ አዘጋጅ ዘንድ ፤

ወታብእ ለአቡከ ወይብላእ ፤

ለአባትህ አቅርበህለት ይበላ ዘንድ ፤

ከመ ይባርከ ቅድመ እግዚአብሔር ዘእንበለ ይሙት ወትኩን ቡሩከ ፤

ሳይሞት በእግዚአብሔር ፊት ይመርቅህ ዘንድ፤ የተመረቅ ህም ትሆናለህ አለችው።

፳፩፤ ወይቤላ ያዕቆብ ለርብቃ እሙ ኢይምህክ በእንተ ኵሉ ዘይበልዕ አቡየ ፤

ያዕቆብም እናቱ ርብቃን እን ዲህ አላት አባቴ ስለሚበላው ሁሉ እምቢ አልልም ፤

ወያሠምሮ ፤

ደስ የሚአሰኘውን ሁሉ አደር ጋለሁ ፤

ወባሕቱ እፈርህ አነ እምከመ ኢይለቡ ቃልየ ፤

ነገር ግን እናቴ ! ቃሌን እንዳ ይለየው ብዬ እኔ እፈራለሁ፤

ወይፈቅድ ይግሥሠኒ ፤

ሊዳሥሠኝም ይወዳል ፤

ወአንቲ ተአምሪ ከመ አነ ልሙፅ ወኤሳው እኁየ ጸጓር ፤

እኔ ጸጉር እንደሌለኝ ኤሳው ወንድሜ ጠጉር እንዳለው አንች ታውቂአለሽ ፤

ወእከውን ቅድመ አዕይንቲሁ ለአቡየ ።

ከመ ዘያስተአኪ፤

በፊቱ የናቅሁት የአቃለል ኹት ይመስለዋል፤

ወእገብር ግብረ ዘኢአዘዘኒ፤

ያላዘዘኝን የም ሠራ እመስላ ለሁ፤

ወይትመዐዐኒ ይቆጣኛል፤

ወአመጽእ ላዕሌየ መርገመ ወአኮ በረከተ፤

በረከትን ያይደለ መርገምን በላዬ ላይ አመጣለሁ መክ ፈልት ሲሹ መቅሠፍት እን ዲሉ።

፳፪፤ ወትቤሎ ርብቃ እሙ ላዕሌየ ይኩን ዝንቱ መርገምከ ኦወልድየ ዳዕሙ ስማዕ ቃልየ፤

እናቱ ርብቃም ልጄ ሆይ ነገሬን ስማኝ እንጅ መርገምህ በኔ ላይ ይሁን አለችው፤

ወሰምዐ ያዕቆብ ቃለ ርብቃ እሙ፤

ያዕቆብም የእናቱ የርብቃን ቃል ሰማ፤

ወሖረ ወነሥአ ፪ተ መሐስዓ ጠሊ ሠናያነ ወስቡሐነ ፤

ሂዶ ያማሩ የሰቡ የተወደዱ ፪ት የፍየል ጠቦቶችን አመጣ፤

ወአምጽአሙ ለእሙ፤

ወደ እናቱ አመጣቸው፤

ወገብረቶሙ እሙ ዘከመ ያፈቅር፤

እናቱም ይስሐቅ እንደሚ ወደው አድርጋ ሠራቻቸው።

፳፫፤ ወነሥአት ርብቃ አልባሰ ወልዳ ኤሳው ዘይልህቅ ወዘይ ትፈቶ ዘሀሎ ኀቤሃ ውስተ ቤታ፤

በቤቷ በሷ ዘንድ ያለ የሚወደድ የታላቁ ልጇ የኤ ሳውን ልብስ ርብቃ አመ ጣች፤

ወአልበሰቶ ለያዕቆብ ወልዳ ዘይ ንዕስ፤

ታናሹ ልጇን ያዕቆብን አለበ ሰችው፤

ወአምእስተ መሐስአ ጠሊ አንበረት ዲበ እደዊሁ፤

የፍየሉን ጠቦት ቁርበት በጁ ላይ አኖረች፤

ወውስተ ዕርቃነ ሥጋሁ ወክሣዱ፤

አንገቱን ዕርቃነ ሥጋውን አለበሰችው፤

ወወሀበቶ ተብሲለ ወኅብስተ ወዘገ ብረት ውስተ እደ ያዕቆብ ወልዳ፤

ያዘጋጀችውን ንፍሮውን ዳቦ

ውን በልጇ ያዕቆብ እጅ አደረ ገች።

፲፱፤ወቦአ ኀበ ይስሐቅ አቡሁ፤

ወደ አባቱ ወደይስሐቅ ገባ፤

ወይቤ አነ ወልድከ ገበርኩ በከመ ትቤለኒ፤

እኔ ልጅህ እንዳዘዝሽኝ አደረግሁ፤

ተንሥእ ወንበር ወብላዕ እምዘ አሥገርኩ አባ ከመ ትባርከኒ ነፍስከ፤

ተነሥተህ ተቀምጠህ አባቴ ሰውነትህ ትመርቀኝ ዘንድ አድኜ ከአመጣሁት ብላ፡ አለው።

፳፤ወይቤሎ ይስሐቅ ለወልዱ ምንት ከመዝ ዘአፍጠንከ ረኪበ ወልድየ፤

ይስሐቅም ልጁ እንዲህ ፈጥነህ ያገኘህበት ምክንያት ምንድነው? አለው፤

ወይቤ ያዕቆብ ዘአርከበኒ አምላክከ ቅድሜየ፤

ያዕቆብም፤ በፊትህ ፈጥኖ ያስገኘልኝ ፈጣሪህ ነው አለ።

፳፩፤ወይቤሎ ይስሐቅ ቅረብ ወእግሥሥከ ወልድየ፤

ይስሐቅም ልጁ ቅረብ ልዳስ ስህ አለው፤

እመ አንተኑ ወልድየ ኤሳው ወእመ ኢኮንከሁ፤

አንተ ልጄ ኤሳው እንደሆንኽ አይደለህም እንደሆነ አውቅ ዘንድ።

፳፪፤ወቀርበ ያዕቆብ ኀበ ይስሐቅ አቡሁ ወገሠሦ፤

ያዕቆብም ወደአባቱ ይስሐቅ ቀረበ ዳሰሰው፤

ወይቤ ቃልከሰ ቃለ ያዕቆብ ወእደ ውሰ አዕዳወ ኤሳው፤

ቃልህ የያዕቆብን ቃል ይመስ ላል፤እጅህ ግን የኤሳውን እጅ ይመስላል።

፳፫፤ወኢያእመሮ፤

አላወቀውም፤

እስመ ሚጠት ውእቱ እምሰማይ ለአሕልፎ መንፈሱ፤

ከእግዚአብሔር ታዝዞ ልቡ ናው ወደ ያዕቆብ የሚመለ ስበት ጊዜ ነውና።

፳፬፤ወኢያእመረ ይስሐቅ እስመ እደዊሁ ከመ እደወ ኤሳው ጸጓር ከመ ይባርኮ፤

ይመርቀው ዘንድ እጆቹ እንደ ኤሳው እጆች ጠጉራም ሁነዋ ልና ይስሐቅ አላወቀውም።

፴፤ወይቤ አንተኑ ኤሳው ወል ድየ ፤

አንተ ልጄ ኤሳው ነህን አለ፤

ወይቤሎ እወ አነ ወልድከ፣

አዎን እኔ ልጅህ ነኝ አለው፤

ወይቤ አቅርብ ሊተ ወእብላዕ እምዘ አሥገርከ ወልድየ ከመ ትባርከ ነፍስየ፤

ልቡናየ እንድትመርቅህ አድ ነህ ከአመጣኸው እበላ ዘንድ አቅርብልኝ አለው።

፴፩፤ወአቅረበ ሎቱ መብልዐ ወበልዐ፣

መብሉን አቀረበለት በላ፣

ወአብእ ሎቱ ወይነ ወሰትየ፤

ወይኑን አቀረበለት ጠጣ።

፴፪፤ወይቤሎ ይስሐቅ አቡሁ ቅረበኒ ወሰዐመኒ ወልድየ ፤

አባቱ ይስሐቅም ልጄ ቀርበህ ሳመኝ አለው።

፴፫፤ወቀርበ ወሰዓሞ፤

ቀርቦ ሳመው፤

ወአጼነወ ጼና አልባሲሁ ምዑዘ ወባረኮ፣

ደስ የሚያሰኝ የልብሱን መዓዛ አሽቶ መረቀው፤

ወይቤ ናሁ ጼና አልባሲሁ ለወልድየ፣ ከመ ጼና ገዳም ዘባረኮ እግዚአብሔር ፣

እነሆ የልጄ መዓዛ እግዚአ ብሔር እንደባረከው ምድረ በዳ መዓዛ ነው አለ ፤

ወየሀብከ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር ይስጥህ፤

ወያብዝኅከ እምጠለ ሰማይ ወእም ጠለ ምድር፤

ከሰማይ ከምድር በተገኘ በረ ከት ያክብርህ ፤

ወብዝኃ ሥርናይ ወቅብዕ ያብዝኅ ለከ፤

ከስንዴ ከዘይት የሚገኘውን በረከት ያብዛልህ አለው።

፴፬፤ ወይትቀነዩ ለከ አሕዛብ ወይሰግዱ ለከ ሕዝብ፣

አሕዛብ ይገዙልህ ሕዝቡም ይስገዱልህ፤

ወኩን እግዚአ ለእኁከ፤

ለወንድምህ፣ ጌታ ሁን፤

ወይስግዱ ለከ ውሉደ እምከ፤

የናትህ ልጆች ሁሉ ይስገዱ ልህ፣

ወኵሉን በረከታት ዘባረከኒ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር የመረቀኝ ምርቃት ሁሉ፤

ወባረኮ ለአብርሃም አቡየ፣

አባቴ አብርሃምን የመረቀው ምርቃት፤

ይኩና ለከ ወለዘርዕከ እስከ ለዓለም፣

ላንተ ለልጆችህ ለዘላለም ይሁን፤

ወዘይረግመከ ርጉም፣

የሚረግምህ ርጉም ይሁን፣

ወዘይባርከከ ቡሩክ ፤

የሚመርቅህ ብሩክ ይሁን።

፴፭፤ ወኮነ እምድኅረ አኅለቀ እንዘ ይባርኮ ይስሐቅ ለወልዱ ያዕቆብ፣

ይስሐቅ ልጁ ያዕቆብን መርቆ ከጨረሰ በኋላ እንዲህ ሆነ።

፴፮ ወኮነ እምድኅረ ወፅአ ወፂአ ያዕቆብ እምይስሐቅ አቡሁ ተኃብአ፤

ያዕቆብም ካባቱ ይስሐቅ ተለይቶ መውጣትን ከወጣ በኋላ ተሰወረ፤

ወኤሳውሰ እኁሁ በጽሐ እምንዒው፣ ወንድሙ ኤሳው ግን ከአደን መጣ ፤

ወገብረ ውእቱኒ መብልዐ፣

እሱም ምግቡን አዘጋጀ፤

ወአብአ ለአቡሁ፣

ላባቱ አቀረበ፣

ወይቤሎ ለአቡሁ ተንሥእ አቡየ ወብላዕ እምአሥግሮትየ፣

አባቱን እንዲህ አለው አባቴ! ተነሥ አድኜ ካመጣሁት ብላ፤

ከመ ትባርከኒ ነፍስከ፤

ልቡናህ ትመርቀኝ ዘንድ።

፴፯፤ ወይቤሎ ይስሐቅ አቡሁ መኑ አንተ፤

አባቱ ይስሐቅም አንተ ማነህ አለው፤

ወይቤሎ አነ በኵርከ ኤሳው ወልድከ ገበርኩ በከመ አዘዝከኒ፤

እኔ የበኸር ልጅህ ኤሳው ነኝ፤ እንዳዘዝከኝ አደረግኹ አለው።

፴፫፤ ወተደመ ይስሐቅ ድማመ ዓቢየ ጥቀ፤

ይስሐቅም ፈጽሞ ተደነቀ፤

ወይቤ ይስሐቅ መኑ ውእቱ ዝንቱ ዘነዐወ ወአሠገረ ሊተ ወአምጽአ፤

አድኖ አጥምዶ ያመጣልኝ ይህ ማነው? አለ፤

ወበላዕኩ እምኵሉ ዘእንበለ ትምጻእ አንተ ወባረክዎ፤

አንተ ሳትመጣ ከሁሉ በልቼ የመረቅሁት ማነው? ቡሩክ ይኩን፤ የተባረከ ይሁን፤

ወኵሉ ዘርዑ እስከ ለዓለም ፤

ልጁ ሁሉ ለዘላለም የተባረከ ይሁን አለ።

፴፱፤ ወኮነ ሶበ ሰምዐ ኤሳው ነገረ አቡሁ ይስሐቅ ጸርሐ በቃል ዓቢይ ወመራር ጥቀ፤

ኤሳው ያባቱን ነገር በሰማ ጊዜ እንዲህ ሆነ እጅግ በሚያሳዝን በጽኑ ቃል ጮኸ፤

ወይቤሎ ለአቡሁ ባርከኒ ኪያየኒ አባ፤

አባቴ እኔንም መርቀኝ አለው።

፵፤ ወይቤሎ አቡሁ መጽአ እኁከ በሕብል ወነሥአ በረከታቲከ፤

ወንድምህ በተንኮል መጥቶ በረከትህን ሁሉ ወሰደብህ።

ወአብልአኒ ወአስተየኒ ወነሥአ በረከታቲከ ፤

አበላኝ አጠጣኝም በረከቶችህንም ወሰደ አለው፤

፵፩፤ ወይቤ ኤሳው ይእዜ አእመርኩ በዘተሰምየ ስሙ ያዕቆብ አእቀጸኒ ፪ኤ ጊዜ፤

ያዕቆብ ተብሎ በተጠራበት ስሙ ሁለት ጊዜ እንዳሰናከለኝ ዛሬ አወቅሁ፤

ናሁ ዝ ዳግሙ ፤

እነሆ ይህ ሁለተኛው ነው፤

ቀዳሚ ልደትየ ነሥአኒ ፤

አስቀድሞ ብኵርናየን ወሰደ፤ ወይእዜኒ ነሥአኒ በረከትየ፤ ዛሬም በረከቴን ወሰደብኝ፤

ወይቤ ኢያትረፍከኑ ሊተ በረከተ አባ፤

አባቴ በረከትህን ለእኔ አላተረፍኸልኝምን አለ።

፴፯፤ወአውሥአ ይስሐቅ ወይቤሎ ለኤሳው፤

ይስሐቅም መልሶ ኤሳውን እንዲህ አለው፣

ናሁ እግዚአ ሤምክዎ ለከ ፣

እንሆ ባንተ ላይ ጌታ አድርጌ ሾምሁት፣

ወኵሎሙ አኃዊሁ ወሀብክዎ ሎቱ አግብርቲሁ ይኩንዎ፤

ወንድሞቹ ሁሉ የእሱ ተገዥ ዎች ይሆኑ ዘንድ ሰጠሁት፣

ወበብዝኃ ሥርናይ ወወይን ወቅ ብዕ አጽናእክዎ፤

ዘይቱን ወይኑን ስንዴውን፣ በማብዛት አከበርሁት፣

ወለከ ምንተ እሬሲ ወልድየ ይእዜ፣

ልጄ ዛሬ ላንተ ምን ላድርግ ልህ? አለው።

፴፰፤ወይቤሎ ኤሳው ለይስሐቅ አቡሁ አሐቲኑ ክመ በረከትከ እን ቲአከሰ አባ፣

ኤሳውም አባቱ ይስሐቅን አባቴ የአንተስ በረከትህ አን ዲት ብቻ ናት? አለው፤

ባርክኒ ኪያየኒ አባ፤

አባቴ! እኔንም መርቀኝ፤

ወአንሥአ ቃሎ ኤሳው ወበከየ፤

ኤሳውም ቃሉን አሰምቶ ጮኸ።

፴፱፤ወአውሥአ ይስሐቅ ወይቤሎ፤

ይስሐቅም መልሶ እንዲህ አለው፣

ወናሁ እምጠለ ምድር ይኩን ንብ ረትከ፤

እንሆ በረከትህ ከምድር የሚ ገኘው ይሁን፣

ወእምጠለ ሰማይ እምላዕሉ፤

ከምድርም በላይ ካለ ሰማይ የሚገኘው ይሁን፣

ወበመጥባሕትከ ተሐዩ፤

ገለህ፣ ስልበህ፣ ኑር፣

ወተቀነይ ለእኁከ፤

ለወንድምህ ተገዛ፣

ወይኩን እግዚአከ፣

ጌታህ ይሁን።

፵፤ወእመ ዐበይከ ወአሰሰልከ አርዑቶ እምክሳድከ፣

አልገዛም ብትል አገዛዙን

ከአንተ ብታርቅ፣

አሜሃ ትኤብስ ኵሎ አበሳ ዘለሞት፣

ለሞት የሚአበቃ በደል ትበድላለህ፣

ወይሜረዉ ኵሉ ዘርዕከ እምታሕተ ሰማይ፤

ልጆችህ ሁሉ ከሰማይ በታች ከዚህ ዓለም ይጠፋሉ፣

ወይትሜዐከ ኤሳው ያዕቆብሃ በእንተ በረከት እንተ ባረኮ አቡሁ፤ አባቱ ስለ መረቀው ምርቃት ኤሳው ያዕቆብን ይቆጣው ነበር።

፴፮፤ ወይቤ ኤሳው በልቡ ይእዜኒ ይበጽሕ መዋዕለ ላሁ ለአቡየ ወእቀትሎ ለያዕቆብ እኁየ፣

ኤሳውም በልቡ አባቴ የሚሞትበት ቀን አሁን ደርሶልኝ ወንድሜ ያዕቆን ገድየው ይል ጀመር፤

ወነገራ መልአክ ለርብቃ በሕልም ነገሮ ለኤሳው ወልዳ ዘይልህቅ፤

የታላቁ ልጇን የኤሳውን ነገር በሕልም መልአክ ለርብቃ ነገራት።

፴፯፤ ወፈነዊዋ ርብቃ ጸውዐቶ ለያዕቆብ ወልዳ ዘይንዕስ፤

ርብቃ በእጇ ጠቅሳ ታናሹ ልጇ ያዕቆብን ጠራችው፣

ወትቤሎ ናሁ ኤሳው እኁከ ይትቄየመከ ከመ ይቅትልከ፣

ይገድልህ ዘንድ ወንድምህ ኤሳው እነሆ ቂም ይዞብሃል፣

ወይእዜኒ ወልድየ ስምዐኒ ቃልየ፣

አሁንም ልጄ ነገሬን ስማኝ፤

ተንሥእ ወጕየይ ወሑር ኀበ ላባ እኁየ ካራንሃ፣

ተነሥተህ ከወንድሜ ላባ ዘንድ ወደ ካራን ሂድ፣

ወንበር ምስሌሁ ሕዳጠ መዋዕለ እስከ ይትመየጥ መዓተ እኁከ፤

የወንድምህ ቁጣ እስኪበርድ ድረስ ጥቂት ቀን ከሱ ጋራ ተቀመጥ፤

ወየሐድግ መዓቶ እምኔከ፤

ከአንተ ቁጣውን እስኪተው ድረስ፣

ወይረሥእ ኵሎ ዘመጠነ ረሰይከ፣

ያደረግኸውን ሁሉ እስኪረሳ ድረስ፣

ወፈኒውየ እምህየ እትቄበለከ፣

ሰው ሰድጀ ከዚያ እቀበልህ አለሁ አለችው።

፴፰፤ወይቤ ያዕቆብ ኢይፈርህ እመ ፈቀደ ይቅትለኒ አቀትሎ፤

ያዕቆብም አልፈራም አለ ሊገ ድለኝም ቢወድ እገድለዋለሁ አለ።

፴፱፤ወትቤሎ አኮ ወልድየ ሐር ከመ ኢይምክን እምክልኤክሙ ውሉድየ በአሐቲ ዕለት፤

ልጄ በአንዲት ቀን ሁለታች ሁን እንዳላጣ ሂድ አለችው።

፵፤ወይቤላ ያዕቆብ ለርብቃ እሙ፤

ያዕቆብም እናቱ ርብቃን እን ዲህ አላት፤

ናሁ ተአምሪ ከመ ረሥአ አቡየ ወኢይሬኢ፤

እነሆ አባቴ አርጅቶ እንደማ ያይ ታውቂያለሽ፤

እስመ ከብዳ አዕይንቲሁ፤

አይኖቹ ፈዘዋልና።

፵፩፤ወእመኒ ኃደግዎ እኩይ ውእቱ በቅድመ አዕይንቲሁ፤

ትቼው ብሄድም በፊቱ ክፉ ነገር ነው ፤

እስመ አኀድሳ ወአሐውር እም ኔከሙ፤

ከእናንተ ተለይቼ ትቼው ስለ ሔድኩ፤

ወይትመአዕ ላዕሌየ አቡየ፤

አባቴ ተቆጥቶ፤

ወይረግመኒ፤

ይረግመኛልና፤

ኢየሐውር፤

አልሔድም፤

ወእመሰ ውእቱ ፈነወኒ ባሕቲቱ እሐውር አሜሃ፤

ከኔ ከአሰናበተኝ ግን ያን ጊዜ እሄዳለሁ።

፵፪፤ ወትቤሎ ርብቃ ለያዕቆብ አነ እበውእ ወእነግሮ ለአቡከ ወይፌን ወከ፤

ርብቃም ያዕቆብን እኔ ገብቼ ለአባትህ እነግረዋለሁ ያሰናብ ትሃል አለችው።

፵፫፤ ወቦአት ርብቃ ኀበ ይስሐቅ፤

ርብቃም ከይሐቅ ዘንድ ገብታ፤

ወትቤሎ ለይስሐቅ ግዕዝኩ ሕይ ወትየ እምክልኤሆን አዋልደ ኬጢ

ዘከነዓን እለ ነሥአ ሎቱ ኤሳው አንስትያ፤

ይስሐቅን እንዲህ አለችው፣ ኤሳው ሚስት አድርጎ ካገ ባቸው ከኬጢ ልጆች ከሁለቱ የተነሣ ኑሮየን ጠላሁ፤

ወእመ ነሥአ ያዕቆብ ብእሲተ እምውስተ አዋልደ ምድር ዘከነዓን እለ ከመ እላ ለምንት ሊተ እንከ እሐዩ፤

ያዕቆብ ለራሱ ከከነኣን ምድር ልጆች ሚስት ካገባ እንደነዚያ ከሆኑ እንግዲህ እንደምን እኖ ራለሁ፤

እስመ እኩያት እማንቱ አዋልደ ምድረ ከነአን ፤

የከነአን ሴቶች ልጆች ክፉ ዎች ናቸውና ።

፶፬፤ወፀውዐ ይስሐቅ ያዕቆብሃ ወልዶ፤

ይስሐቅም ልጁ ያዕቆብን ጠርቶ፤

ወባረኮ ወገሠፆ፤

መረቀው መከረው፣

ወይቤሎ ኢትንሣእ ለከ ብእሲተ እምዙሎን አዋልደ ከነአን፣

ከከነአን ልጆች ወገን ሚስትን አታግባ፣

ተንሥእ ወሑር ውስተ መስጴጦምያ ቤቶ ለባቱኤል አቡሃ ለእምከ፤

ከናትህ አባት ከባቱኤል ወገን ወደ ሚሆን ሶርያ ተነሥተህ ሂድ።

፶፭፤ወንሣእ ለከ በህየ ብእሲተ እምአዋልደ ላባ እትሁ ለእምከ፤

ከናትህ ወንድም ከላባ ልጆች ሚስትን አግባ፤

ወአምላከ ሰማይ ይባርከ ወያልሕቀ ወያብዝኀከ፣

ሰማይን የፈጠረ አምላክ ያክ ብርህ ፈጽሞ ያብዛኀ፣

ወኩን መክብበ ለአሕዛብ፤

የአሕዛብ ገዥ ሁን፣

ወየሀብከ በረከታቲሁ ለአቡየ አብር ሃም ለከ፤

የአባቴ የአብርሃምን ምርቃት ሁሉ ላንተ ይስጥህ፤

ወለዘርዕከ እምድኅሬከ፤

ካንተም በኋላ ለልጅህ ይስ ጠው፣

ከመ ትረሳ ለምድረ ፍልሰትከ፣

ይህቺውም ከነዓን ናት፣ ተሰደህ ትኖርባት የነበረችውን አገር ትወርሳት ዘንድ፤

ወኵላ ምድረ እንተ ወሀቦ እግዚአብሔር ለአብርሃም፤

እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን አገር ሁሉ ይስጥህ ፤

ሑር ወልድየ በሰላም፤

ልጄ! በተድላ በደስታ ሂድ አለው፡፡

፳፮፤ ወፈነዎ ይስሐቅ ለያዕቆብ፣

ይስሐቅም ያዕቆብን አሰናብቶ ሰደደው፤

ወሖረ ያዕቆብ መስጴጦምያ ኀበ ላባ ወልደ ባቱኤል ሶርያዊ እኁሃ ለርብቃ እሙ ለያዕቆብ፣

ከያዕቆብ እናት ርብቃ ወንድም ከሶርያ ሰው ከባቱኤል ልጅ ከላባ ዘንድ ወደ ሶርያ ሄደ፡፡

፳፯፤ ወኮነ እምድኅረ ተንሥአ ያዕቆብ ለሐዊር መስጴጦምያ፤

ያዕቆብም ወደሶርያ ለመሄድ ከተነሣ በኋላ፣

ኀዘነ መንፈሳ ለርብቃ ድኅረ ሖረ ወልዳ፤

ልጇ ያዕቆብ ከሄደ በኋላ የርብቃ ልቡናዋ አዘነ፤

ወትበኪ፣

ታለቅስ ጀመር፡፡

፳፰፤ ወይቤላ ይስሐቅ ለርብቃ እኅትየ ኢትብክዪ በእንተ ያዕቆብ ወልድየ፤

ይስሐቅም ርብቃን እንዲህ አላት እኅቴ ስለ ልጄ ያዕቆብ አታልቅሽ አላት፤

እስመ በሰላም የሐውር ወበሰላም ይትመየጥ፤

በደህና ሂዶ በደህና ይመለሳልና፤

ወአምላክ ልዑል የአቅቦ እምኵሉ እኩይ፤

ገናናው፣ አምላክ ከመከራው ሁሉ ይጠብቀዋልና፤

ወይሄሉ ምስሌሁ፣

ከሱ ጋራ በረድኤት ጸንቶ ይኖራልና፤

እስመ ኢየኀድጎ ኵሎ መዋዕሊሁ፤

ባለ ዘመኑ ሁሉ አይለየውምና፤

እስመ አእምር ከመ ይሤራህ ፍናዊሁ በኵሉ ኀበ ሖረ እስከ አመ ይገብዕ በሰላም ኀቤነ፣

ወደኛ በደህና እስኪመለስ ድረስ በሄደበት ሁሉ ጐዳና ውን እንዲያቀናለት አውቃ ለሁና።

፶፱፤ወንሬእዮ በሰላም፤

በደህና እናየዋለን፤

ኢትፍርሂ በእንቲ እሁ እኅትየ፤

እኅቴ አንቺ ስለ እሱ አት ፍሪ፤

እስመ ራትዕ በፍኖቱ ውእቱ፤

እሱ በሥራው ሁሉ ቅን ነውና፤

ወፍጹም ውእቱ፤

ፍጹም ነውና፤

ወብእሲ ምእመን ውእቱ፤

የታመነ ሰው ነውና፤

ወኢይትገደፍ ኢትብከዪ፤

በመከራ አይወድቅምና፤ አታ ልቅሽ አላት፤

ወይናዝዛ ይስሐቅ ለርብቃ በእንተ ያዕቆብ ወልዳ፤

ይስሐቅም ስለ ልጇ ያዕቆብ፤ ርብቃን ያረጋጋት ነበር፤

ወባረኮ፤

መረቀው ፡፡

## ምዕራፍ ፳

፩፤ወወጽአ ያዕቆብ እምዓዘቅተ መሐላ ከመ ይሑር ካራንሃ፤

ያዕቆብም ወደ ካራን ይሄድ ዘንድ ከቤርሳቤህ ወጣ፤

በዓመት ቀዳሚ ዘሱባዔ ካልዕ ዘ፵ወ፬ቱ ኢዮቤልዩ፤

በሁለተኛው ሱባኤ በመጀመር ያው ዓመት ባርባ አራተኛው ኢዮቤልዩ፤

ወበጽሐ ውስተ ሎዛ እንተ ውስተ ደብር፤

በተራራ ካለች ሎዛ ደረሰ፤

እንተ ይእቲ ቤቴል ፤

ይህችውም ቤቴል ናት።

፪፤በሠርቀ ወርኀ ቀዳሚ ዘዝ ሱባዔ፤

በዚህ ሱባኤ በመጀመርያው ወር በሚያዝያ፤

ወበጽሐ መካነ መስዮ፤

ከሚያአድርበት ሎዛ በመሸ ጊዜ ደረሰ፤

ወተግህሠ እምፍኖተ ዓረቢሃ ለመንገድ፤

ወንድሜ ቢከተለኝ፤ ጠላት